አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

አራተኛ ዓመት ቁጥር ፴፭
አዲስ አበባ ሐምሌ ፪ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም.

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Fourth Year No. 35
ADDIS ABABA 9th of July, 2012

***ማውጫ***

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር አስፈጻሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላትን እንደገና ለማቋቋም የወጣ አዋጅ**

***CONTENTS***

***The Addis Ababa City Government Executive and Municipal Service Organs Re-establishment Proclamation***

***አዋጅ ቁጥር ፴፭/፪ሺ፬ ዓ.ም.***
***የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ***

የአዲስ አበባ ከተማ ከጊዜ ወደ ጊዜ በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና ፖለቲካዊ ረገድ ዕድገት ያስመዘገበ በመሆኑና ከሚመዘገበዉ ለዉጥ ጋር አብሮ የሚሄድ የከተማዉ አስተዳደር የአስፈጻሚና ማዘጋጃ ቤ ዊ አገልግሎት አካላትን አደረጃጀት መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ፤

አገራዊ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ለማሳካትና የከተማዉ አስተዳደር የሚያከናዉናቸዉን ዘርፈ ብዙ የልማት ሥራዎች ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር በተለያዩ መስኮች የሚታዩ ክፍተቶችንና ችግሮችን መቅረፍ እንዲቻል አንዱ መፍትሄ የተቋማትን አደረጃጀት እንዲሁም ሥልጣንና ተግባራትን መወሰን በመሆኑ፣

***Proclamation No. 35/2012***
***The Addis Ababa City Government Executive and Municipal Service Organs Re-establishment Proclamation***

**WHEREAS**, the Addis Ababa City is developing from time to time in the economic, political and social aspects and it is found necessary to create organizational structure of the executive and municipality services organs which is compatible to the level of development of the City;

**WHEREAS**, it is believed that one of the possible solutions to be successful in the national growth and transformation plan and to transform to better level the development activities of the City and alleviate the gaps and problems observed in the different sectors of the City Government is determining the organization as well the power and function thereof;

ያንዱ ዋጋ
Unit price

www.chilot.me

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፳፬፻፵፭
**Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445**

የከተማዉን አስተዳደር አስፈጻሚና ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አካላት የተቋቋሙበት አዋጅ ቁጥር 15/2001 በተደጋጋሚ የተሻሻለ በመሆኑና ለተገልጋዮች አመቺ እንዲሆን አንድ ወጥ በሆነ ህግ ማካተቱ ተገቢ በመሆኑ፤

የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ ዓ.ም. ( ንደተሻሻለ) አንቀጽ ፲፬/፩/ሀ/ መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

**፩ አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ «የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚና ማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት ንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፴፭/፪ሺ፬» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪ ትርጓሜ**

በዚህ አዋጅ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ስካልሆነ ድረስ፡-

፩ «ከተማ» ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤

፪ «አስተዳደር» ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፫ «ቻርተር» ማለት የተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ ዓ.ም ነው፤

፬ «ከንቲባ» ማለት በቻርተሩ አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፪/፫/ ንደተተረጎመ አስተዳደሩን የሚመራ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ነው፤

፭ «ምክትል ከንቲባ» ማለት በቻርተሩ አንቀጽ ፳፪ የተመለከተው የከተማው አስተዳደር አስፈጻሚ ነው፤

**WHEREAS**, it is found proper to consolidate into a single proclamation both proclamation No. 15/2009, that established the executive and municipal organs of the City Government, and the amendments thereof with the view to create conducive condition for customers;

**NOW,THEREFORE,** in accordance with Article 14(1)(a) of the Addis Ababa City Government Revised Charter Proclamation No 361/2003 it is hereby proclaimed as follows: -

## *PART ONE*
## *GENERAL*

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Addis Ababa City Government Executive and Municipal Service Organs Re-establishment Proclamation No 35/2012''

**2. Definitions**

In this Proclamation, unless the context demands otherwise:-

1. **" City''** means the Addis Ababa City;
2. **"Government''** means the Addis Ababa City Government;
3. **"Charter''** means the Addis Ababa City Government Revised Charter Proclamation No. 361/2003:
4. **"Mayor''** means the Chief Executive Officer of the City Government as stated under Article 2(3) of the Charter Proclamation No. 361/2003;
5. **"Deputy Mayor''** means the executive official of the City Government mentioned under Article 22 of the Charter;

፮ «ቢሮ» ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬/፩/ የተመለከተዉ የአስተዳደሩ አስፈጻሚ አካል ነው፣

፯ «ካቢኔ» ማለት በቻርተሩ አንቀፅ ፲/፩/ /ሐ/ የተመለከተውና በቻርተሩ አንቀጽ ፳፫ የተደነገጉት ስልጣንና ተግባሮች ያሉት የአስተዳደሩ የስልጣን አካል ነው፣

፰ «የከተማ ምክር ቤት» ማለት በቻርተሩ አንቀጽ ፲/፩/ሀ/ የተመለከተውና ስልጣንና ተግባሮቹ በአንቀፅ ፲፬ የተዘረዘሩት የአስተዳደሩ የስልጣን አካል ነው፣

፱ «ክፍለ ከተማ» ማለት በቻርተሩ አንቀጽ ፪(፭) የተመለከተው የከተማው ሁለተኛ ደረጃ የአስተዳደር ርከን ነው፣

፲ «የወረዳ አስተዳደር» ማለት የክፍለ ከተማ አካል የሆነ የከተማው ሶስተኛ ደረጃ የአስተዳደር ርከን ነው፣

፲፩ «የክፍለ ከተማ ዋና ሥራ አስፈፃሚ፣ የክፍለ ከተማ ሥራ አስኪያጅና የክፍለ ከተማ ቋሚ ኮሚቴ» ማለት ንደቅደም ተከተላቸው በቻርተሩ አንቀጽ ፴፬ ስከ ፴፯ የተመለከቱት አካላት ናቸው

፲፪ «የወረዳ ዋና ሥራ አስፈጻሚ፣ የወረዳ ቋሚ ኮሚቴ የወረዳ ስራ አስኪያጅ» ማለት ንደቅደም ተከተላቸው በቻርተሩ አንቀጽ ፴፰(፪) የተመለከቱት የወረዳ አካላት ናቸው::

## ክፍል ሁለት
## ስለ ካቢኔ አባላትና ስለ ሌሎች አስፈጻሚ አካላት
### ምዕራፍ አንድ
### የካቢኔ አባላትና የሌሎች አስፈጻሚ አካላት መቋቋምና አደረጃጀት

፫ የካቢኔ አባላት

፩ የከተማ አስተዳደሩ ካቢኔ አባላት የሚከተሉት ናቸው:-

ሀ. ከንቲባው

6. **"Bureau''** means the executive organ of the Government mentioned under Article 4 (1) of this Proclamation;

7. **"Cabinet''** means organ of power of the City Government stated under Article 10(1)(c) of the Charter and whose powers and functions are stated under Article 23 of the Charter;

8. **"City Council''** means organ of power of the City Government mentioned under Article 10(1)(a) and 9whose powers and functions are stated under Article 14 of the Charter;

9. **"Sub-City''** means the second administrative stratum of the City mentioned under Article 2(5) of the Charter;

10. "**Wereda Administration**" means the third administrative stratum of the City, which is a unit of Sub-City;

11. **"Chief Executive of a Sub-City, Sub-City Manager, and Standing Committee of a Sub-City''** means organs mentioned in Articles 34 to 37 of the Charter respectively;

12. **"Chief Executive of Wereda, Standing Committee of Wereda, Wereda Manager''** means executive organs of Wereda mentioned under Article 38(2) of the Charter respectively.

## Part Two
## Cabinet Members and otherexecutive Organs
### Chapter one
### Establishment and Organization of Cabinet Members and Other Executive Organs

**3. Cabinet Members**

1 The Cabinet members of the City Government are the following:

a) the Mayor;

ለ. ምክትል ከንቲባው

ሐ. በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬/፩/ የተቋቋሙትን ቢሮዎች የሚመሩ ላፊዎች፣ ና

መ. ከንቲባው በአባልነት ንዲሳተፉ የሚመርጣቸው የአስተዳደሩ ሌሎች ባለሥልጣኖች::

፪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩/ሐ/ የተመለከተው ማንኛዉም የቢሮ ላፊ በካቢኔው ስብሰባ ላይ ሊገኝ በማይችልበት ጊዜ ምክትሉ ወይም ከአንድ በላይ ምክትሎች ካሉ፣ በግልጽ ተለይቶ ውክልና የተሰጠው ምክትል በካቢኔው ስብሰባ በምትክ አባልነት ይሳተፋል::

**፬ . የቢሮዎችና መሥሪያ ቤቶች መቋቋምና ተጠሪነት**

፩ የሚከተሉት ቢሮዎች ለከንቲባው ተጠሪ በመሆን ህጋዊ ሰውነት ተሰጥቷቸው ንደገና ተቋቁመዋል:-

፩ የአቅም ግንባ ቢሮ፣
፪ የትምህርት ቢሮ፣
፫ የንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ፣
፬ የኮንስትራክሽንና ቤቶች ልማት ቢሮ፣
፭ የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ፣
፮ የጤና ቢሮ፣
፯ የፍትህ ቢሮ፣
፰ የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ቢሮ
፱ የመንገድና ትራንስፖርት ቢሮ፣
፲ የሴቶች ህጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮ፣
፲፩ የባህልና ቱሪዝም ቢሮ፣
፲፪ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ፣
፲፫ የኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ፤ እና
፲፬ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ

b) the Deputy Mayor;

c) the Heads of Bureaus established in accordance with Article 4(1) of this Proclamation; and

d) Other officials of the Government selected by the Mayor to be members in the Cabinet.

2. Where the Bureau head mentioned in sub-article (1) (c) of this Article is unable to attend the Cabinet meeting, the deputy or where there are more than one deputies, the deputy specifically designated shall be a substitute member and attend the Cabinet meeting.

**4. Establishment and Accountability of Bureaus and Offices**

1. The following Bureaus that are accountable to the Mayor are re-established having a legal personality:

1. Bureau of Capacity Building;
2. Bureau of Education;
3. Bureau of Trade and Industry Development;
4. Bureau of Construction and Housing Development;
5. Bureau of Finance and Economic Development;
6. Bureau of Health;
7. Bureau of Justice;
8. Land Development and Management Bureau;
9. Road and Transport Bureau;
10. Bureau of Women, Children and Youth Affairs;
11. Bureau of Culture and Tourism;
12. Bureau of Labour and Social Affairs;
13. Bureau of Communication Affairs; and
14. Micro and Small Scale Enterprises Development Bureau;

፪. የሚከተሉት ሌሎች የአስተዳደሩ አስፈፃሚ አካላት ተጠሪነ ቸው ለከንቲባው ሆነው ሕጋዊ ሰውነት ተሰጥቷቸው ንደገና ተቋቁመዋል:-

ሀ/ የከንቲባ ጽህፈት ቤት፣

ለ/ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን፣

ሐ/ የከተማው ሥራ አስኪያጅ፣

መ/ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ፣

ሠ/ የገቢዎች ባለሥልጣን፣ እና

ረ) የአዲስ አበባ ከተማ ስፖርት ኮሚሽን::

## ፭ የሌሎች አስፈጻሚ አካላትና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ንደገና መቋቋም

በሌሎች አግባብነት ባላቸዉ ህጎች የተደነገገዉ ንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት የአስተዳደሩ አስፈፃሚ አካላትና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሕጋዊ ሰውነት በማግኘት ንደገና ተቋቁመዋል:-

፩ የሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ፣

፪ የሥራ አመራር ኢንስቲትዩት፣

፫ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ልማት ኤጀንሲ፣

፬ የቤቶች ልማትና አስተዳደር ኤጀንሲ፣

፭ የቤቶች ግንባታ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት፣

፮ የመንግስት ግንባታዎች ኤጀንሲ፣

፯ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማትና ቁጥጥር ባለሥልጣን፣

፰ የህብረተሰብ ተሳትፎ ልማት ኤጀንሲ፣

፱ የ ንጦጦ ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ፣

፲ ጀኔራል ዊንጌት ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ፣

፲፩ የአዲስ አበባ ተግባረ ዕድ ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ ፣

፲፪ ንፋስ ስልክ ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ ፣

፲፫ ምስራቅ ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ ፣

፲፬ የሙያ ብቃት ምዘናና ማረጋገጫ ማዕከል፣

፲፭ አቃቂ ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ፣

2. The following other executive organs of the Government that are accountable to the Mayor are re-established having a legal personality:
   a) Office of the Mayor;
   b) Environmental Protection Authority;
   c) The City Manager;
   d) Technical and Vocational Education and Training Agency;
   e) The Revenue Authority; and
   f) Addis Ababa City Sport Commission.

## 5.Re-establishment of Other Executive Organs and Higher Education Institutions

Notwithstanding the provisions of other relevant laws, the following executive organs and higher education institutions of the Government are re-established being legal persons:

1. Civil Service Agency;
2. Urban Management Institute;
3. Information Communication Technology Development Agency;
4. Housing Development and Management Agency
5. Housing Construction Project Office
6. Government Construction Agecy
7. Construction Industry Development and Regulatory Authority
8. Public Participation Development Agency
9. Entoto polytechnic College;
10. General Winget Polytechnic College;
11. Addis Ababa Tegbareid Polytechnic College;
12. Nefas Silk Polytechnic College;
13. Misrak Polytechnic College;
14. Occupational Competency Assessment and Certification Centre;
15. Akaki Technical and Vocational College;

፲፮ የኢንቨስትመንት ኤጀንሲ፣

፲፯ ኮተቤ መጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል፤

፲፰ ኤች አይ. ቪ. ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽህፈት ቤት፣

፲፱ ራስ ደስ ዳምጠዉ መ ሰቢያ ሆስፒ ል፣

፳ ዳግማዊ ሚኒሊክ ሆስፒ ል፣

፳፩ ጋንዲ መ ሰቢያ ሆስፒ ል፣

፳፪ ዘዉዲቱ መ ሰቢያ ሆስፒ ል፣

፳፫ ዳግማዊ ሚኒሊክ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ፣

፳፬ ከነማ ፋርማሲዎች ድርጅት፣

፳፭ ጥሩነሽ ቤይጂንግ አጠቃላይ ሆስፒ ል፣

፳፮ የደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽህፈት ቤት፣

፳፯ የማህበራዊ ፍርድ ቤቶች የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ጽህፈት ቤት፣

፳፰ ኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ፣

፳፱ የሲኒማ ቤቶች አስተዳደር፣

፴ የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን፣

፴፩ የመሬት ልማትና ከተማ ማደስ ኤጀንሲ፣

፴፪ የመሬት ባንክና ማስተላለፍ ጽህፈት ቤት፣

፴፫ የከተማ ፕላን ኢንስቲቲዩት፤

፴፬ የመሬት መረጃና ቴክኖሎጂ ማዕከል፤

፴፭ የተቀናጀ የመሬት መረጃ ሥርዓት ዝርጋታ ፕሮጀክት ማስተባበርያ ጽህፈት ቤት፤

፴፮ የማይንቀሳቀስ ንብረት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ፣

፴፯ የይዞታ አስተዳደር የሽግግር ጊዜ አገልግሎት ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት፣እና

፴፰ የምር ማነት ማሻሻያ ማዕከል።

**፮. የሌሎች አስፈጻሚ አካላትና ከፍተኛ የትምህርትና ስልጠና ተቋማት ተጠሪነት**

የአስፈፃሚ አካላትና የከፍተኛ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ተጠሪነት ንደሚከተለው ይሆናል፡-

ሀ - በአንቀጽ (፭) ንዑስ አንቀጽ ፩ - ፫ የተመለከቱት አስፈፃሚ አካላት ተጠሪነት ለአቅም ግንባ ቢሮ፣

16. Investment Agency;
17. Kotebe Primary Level Hospital;
18. Office for Control and Prevention of HIV/AIDS;
19. Ras Desta Damtew Memorial Hospital;
20. Menelik II Hspital;
21. Ghandi Memorial Hospital;
22. Zewditu Memorial Hospital ;
23. Menelik II Health Science College;
24. Kenema Pharmacies Enterprise;
25. Tirunesh Beijing General Hospital
26. Office of Code Enforcement Service;
27. Office of the Judicial Administration Council of Social Courts;
28. Kotobe College of Teachers Education;
29. Cinema Halls Administration
30. Building Permit and Control Authority;
31. Land Development and City Renewal Agency;
32. Land Bank and Transfer Office;
33. Urban Plan Institute;
34. Land Information and Technology Centre;
35. Integrated Land Information Installation Coordination Office;
36. Immovable Property Registration and Information Agency;
37. Title Administration Transitional Period Service Project Office; and
38. Productivity Improvement Centre.

**6. Accountability of Other Executive Organs and Higher Education and Training Institutions**

The accountability of other executive organs and higher education institutions shall be as follows:

a. The executive organs mentioned under Sub-articles (1) to (3) of Article 5 shall be accountable to the Bureau of Capacity Building;

ለ. በአንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ ፬ - ፰ የተመለከቱት አስፈፃሚ አካላት ተጠሪነት ለኮንስትራክሽንና ቤቶች ልማት ቢሮ፣

ሐ. በአንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ ፱ - ፲፭ የተመለከቱት ከፍተኛ የትምህርትና ስልጠና ተቋማት ተጠሪነት ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲ፣

መ. በአንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ ፲፮ የተመለከተው አስፈፃሚ አካል ተጠሪነት ለንግድና ኢንደስትሪ ልማት ቢሮ፣

ሠ. በአንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ ፲፯ - ፳፭ የተመለከቱት አስፈፃሚ አካላት ተጠሪነት ለጤና ቢሮ፣

ረ. በአንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ ፳፮ - ፳፯ የተመለከቱት አስፈፃሚ አካላት ተጠሪነት ለፍትህ ቢሮ፣

ሰ. በአንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ ፳፰ የተመለከተዉ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ተጠሪነት ለትምህርት ቢሮ፣

ሸ. በአንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ ፳፱ የተመለከተዉ ተጠሪነት ለባህልና ቱሪዝም ቢሮ፣

ቀ. በአንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ ፴ – ፴፯ የተመለከቱት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለመሬት ልማትና ማኔጅመንት ቢሮ፣

በ. በአንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ ፴፰ የተመለከተዉ አስፈጻሚ አካል ተጠሪነት ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ ይሆናል፡፡

## ፯. የቢሮዎችና የሌሎች አስፈጻሚ አካላት አደረጃጀትና ከክፍለ ከተማ ጋር ያላቸው ተዋረዳዊ ግንኙነት

፩ የ ያንዳንዱ ቢሮ ወይም ሌላ አስፈጻሚ አካል ላፊ፣ ንደአስፈላጊነቱ ምክትል ላፊዎች፣ ሌሎች አግባብ ያላቸው የሥራ ክፍሎችና ለሥራው የሚያስፈልጉ ሠራተኞች የሚኖረው ሆኖ ይደራጃል፤

b. The executive organs mentioned under sub-article (4) to (8) of Article 5 shall be accountable to the Construction and Housing Development Bureau;

c. The executive organs mentioned under Sub-article (9) to (15) of Article 5 shall be accountable to the Technical and Vocational Education and Training Agency;

d. The executive organ mentioned under Sub-Article (16) of Article 5 shall be accountable to the Bureau of Trade and Industry Development;

e. The executive organs mentioned under sub-article (17) to (25) of Article 5 shall be accountable to the Bureau of Health;

f. The executive organs mentioned under sub-article (26) to (27) of Article 5 shall be accountable to the Bureau of Justice;

g. The higher education institution mentioned under Sub-Article (28) of Article 5 shall be accountable to the Bureau of Education;

h. The organ mentioned under sub-article (29) of Article 5 shall be accountable to the Bureau of Culture and Tourism;

i. The executive organs mentioned under sub-article (30) to (37) of Article 5 shall be accountable to the Land Development and Management Bureau;

j. The executive organ mentioned under sub-article (38) of Article 5 shall be accountable to the Micro and Small Scale Enterprises Development Bureau.

## 7. Organization of Bureaus and Other Executive Organs and Vertical Relation with Sub-City

1. Each Bureau or other executive organ shall have a Head, Deputy Head/s as may be necessary and the required units and staff;

፪. የቢሮ ምክትል ኃላፊ ንደአስፈላጊነቱ በቢሮዉ ሥር ካሉት አንዱን የሥራ ሂደት በባለቤትነት ይመራል፤

፫. ቢሮዎች ከሚያስተባብሯቸውና ከሚመሯቸው አስፈጻሚ አካላት ወይም ከሌሎች አስፈጻሚ አካላት ጋር ንደ ህግ፣ ፋይናንስ ግዥና ንብረት አስተዳደር፣ የሰዉ ይል አስተዳደር ያሉ ደጋፊ ሥራ ሂደት አገልግሎቶች በጋራ ሊጠቀሙ ይችላሉ:: ዝርዝሩ የከተማው ካቢኔ በሚያፀድቀው መዋቅራዊ አደረጃጀት መሠረት በከንቲባው በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፤

፬ የየክፍለ ከተማው ጽህፈት ቤት ወይም የሌላ አስፈጻሚ የስራ ክፍል በቻርተሩና በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት ለክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ተጠሪነቱ ንደተጠበቀ ሆኖ ያንዳንዱ ቢሮ ወይም አስፈጻሚ አካል በ ቅድ ዝግጅት፣ በ ቅድ ክንዋኔ ክትትልና ግምገማ፣ በአቅም ግንባ ፣ እንደአግባቡ በውስጥ ዝውውርና በደረጃ ድገት የሰራተኛ አመዳደብና በሌሎች ቴክኒካዊና ሙያዊ ጉዳዮች በየክፍለ ከተማው በተዋረድ በስራው መስክ ከተደራጀው ጽህፈት ቤት ወይም ሌላ የስራ ክፍል ጋር ቀጥተኛና መደበኛ ግንኙነት በማድረግ ይሰራል::

፰. የቢሮዎች፣ የሌሎች አስፈጻሚ አካላትና ከፍተኛ የትምህርትና ስልጠና ተቋማት የበላይ ኃላፊዎች ተጠሪነትና ኃላፊነት

፩. ያንዳንዱ የቢሮ ኃላፊ የሚመራውን ቢሮ ለሚመለከቱ ሥራዎች፣ ፕሮግራሞችና ሕጎች አፈጻጸም ተጠሪነቱ ለከንቲባው ሆኖ፣

ሀ. ቢሮውን የመምራትና የመወከል ኃፊነት ይኖረዋል፤

ለ. የቢሮውን ሥልጣንና ተግባር ሥራ ላይ የማዋል ኃፊነት ይኖረዋል፤

ሐ. ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለሥራ ቅልጥፍናና ውጤ ማነት አስፈላጊ በሆነ መጠን ለበ ች ኃፊዎች በውክልና መስጠት ይችላል፤

2. A Deputy Head of Bureau shall, as may be necessary, coordinate one core process, being process owner, among those within the Bureau;
3. Bureaus, executive organs coordinated by Bureaus and other executive organs may share support services such as legal, finance, purchase and property administration and human resource management; the details shall be determined by the directives of the Mayor based on the organizational structure approved by the Cabinet;
4. Without prejudice to accountability of the Sub-City executive offices or other executive units to the Chief Executive of the Sub-City in accordance with the provisions of the Charter and this Proclamation, each Bureau or executive organ shall operate by establishing regular and direct relationship with the structure in each Sub-City on matters of planning, performance evaluation and follow-up, capacity building, internal staff transfer and promotion, placement of employees and other technical and professional issues, as may be proper.

**8. Accountability and Responsibilities of Head of Bureaus, Other Executive Organs and Higher Education and Training Institutions**

1. Each Bureau Head shall be accountable to the Mayor for the activities, programs and implementation of laws in the Bureau he/she directs and he/she:
   a) shall direct and represent the Bureau;
   b) shall have the responsibility to execute the powers and functions of the Bureau;
   c) may delegate parts of his powers and functions to the lower officials to the extent it is necessary for the efficiency and effectiveness of the operation.

፪. የሌላ አስፈጻሚ አካል ወይም ከፍተኛ የትምህርትና ስልጠ ተቋም ላፊ የሚመራውን አስፈጻሚ አካል ወይም ከፍተኛ የትምህርትና ስልጠና ተቋም ለሚመለከቱ ሥራዎች፣ ኘሮግራሞችና ሕጎች አፈጻጸም ተጠሪነቱ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ ለተመለከተው ቢሮ ወይም የስልጣን አካል ሆኖ፣ የሚመራውን አስፈጻሚ አካል ወይም ከፍተኛ የትምህርትና ስልጠና ተቋም በተመለከተ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)(ሀ-ሐ) የተመለከቱት ላፊነቶች ይኖሩ ል፣

፫. የቢሮ ወይም የሌላ አስፈጻሚ አካል ወይም ከፍተኛ የትምህርትና ስልጠና ተቋም ላፊ በማይኖርበት ወይም የመሥራት ችሎ ውን ባጣ ጊዜ ምክትል ላፊው ተክቶት ይሠራል:: ንደዚሁም በመደበኛ ሁኔ ደግሞ ምክትል ሀላፊዉ በመዋቅራዊ የሥራ ዝርዝር በተመለከተው መሠረት የ ላፊው የቅርብ ረዳት ሆኖ ይሠራል፣

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አስከ (፫) ና በህግ በሌላ ሁኔ የተደነገገው ንደተጠበቀ ሆኖ የ ላፊዎችና የምክትል ላፊዎች የሥራ ሁኔ በከተማው ካቢኔ በሚወጣ ደንብ ይወሰናል::

## ምዕራፍ ሁለት

## የቢሮዎችና የሚያስተባብሯቸው ሌሎች አስፈጻሚ አካላት ወይም ከፍተኛ የትምህርትና ስልጠና ተቋማት ሥልጣንና ተግባር

### *ዘርፍ አንድ*

### *ሁሉም አካላት ስለሚኖራቸዉ ሥልጣንና ተግባር*

**፱. የወል ሥልጣንና ተግባር**

ያንዳንዱ ቢሮ ወይም ሌላ አስፈጻሚ አካል ወይም ከፍተኛ የትምህርትና ስልጠና ተቋም በሥራው መስክ፤

፩. ከፌዴራል መንግሥት ፖሊሲና ሕግ ጋር የሚጣጣም የአስተዳደሩን ፖሊሲና ሕግ ያመነጫል፣ ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣

2. The Head of other executive organ or higher education and training institution shall be accountable to the Bureau or organ of power mentioned under Article 5 of this Proclamation for the activities, programs and implementation of laws in the executive body or higher education and training institution he directs and shall have the responsibilities stated under sub-article (1)(a-c) of this Article;
3. The Deputy Head of Bureau or other Executive Organ or Higher Education and Training Institution shall act in the absence or incapacity of the concerned Head. Besides in the ordinary course of things, the Deputy Head shall be the close assistant of the Head as indicated in the structural job description;
4. Without prejudice to the provisions stated in sub-articles (1–3) of this Article and other laws, conditions of work for Heads and Deputy Heads shall be determined by the regulations the City Cabinet issues.

## Chapter Two

## Powers and Functions of the Bureaus and Other Executive Organs Coordinated by the Bureaus or Higher Education and Training Institutions

### *Section One*

### *Common Powers and Functions*

**9. Common Powers and Functions**

Each Bureau or other executive organ or higher education and training institution in its field of activity shall have the powers and functions to:

1. initiate policies and laws of the Government consistent with the laws and policies of the Federal Government; prepare plans and budget and implement same upon approval;

፪. በፌዴራል መንግሥትና በአስተዳደሩ የወጡ ፖሊሲዎችና ሕጎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፣ መመሪያዎችን ያወጣል፣

፫. ንደአስፈላጊነቱ ምርምርና ጥናት ያከናውናል፣ ስ ትስቲካዊ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያቀነባብራል፣ ለሚመለከ ቸው ያሰራጫል፣

፬. ሠራተኞቹን አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብ ል፣

፭. በጀትና ንብረት በአስተዳደሩ የፋይናንስ አስተዳደር ና የግዥና ንብረት አስተዳደር ሕግ መሠረት ያስተዳድራል፣ በሕግ መሠረት የአገልግሎት ክፍያ ይሰበስባል፤

፮ የአቅም ግንባ ሥራዎችን ያከናውናል፣ የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ኘሮግራምን ያስፈጽማል፤

፯ አግባብ ካላቸው አካላትና የከተማው ነዋሪዎች ጋር በአጋርነት ለመሥራት የሚያስችሉ ስልቶች በመቀየስ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፰ ስለ ሥራ አፈጻጸሙ በየወቅቱ ተጠሪ ለሆነበት አካል ሪፖርት ያቀርባል፤

፱ የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ በህግ መሠረት ንብረት ያስወግዳል፤

፲ በስሙ ውል መዋዋል፣ መክሰስ ወይም መከሰስ ይችላል፤

፲፩ በዚህ አዋጅና በሌሎች ሕጎች የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት በስራ ላይ ያውላል::

2. ensure the enforcement of policies and laws of the Federal and the City Governments; issue directives;
3. undertake studies and researches as may be necessary, collect and organize statistical data and distribute to concerned parties;
4. employ, administer and terminate the employment relationship with the employees in accordance with appropriate law;
5. administer its budget and properties in accordance with the financial and procurement and property administration laws; and collect service fees in accordance with law;
6. perform activities of capacity building and implement the Civil Service Reform Program;
7. design strategies that enable it to work in partnership with the appropriate organs and residents and implement same;
8. submit periodical reports to the organ it is accountable;
9. own property and dispose property as per law;
10. enter into contract, sue or be sued in its own name;
11. exercise powers and functions vested in it by this Proclamation and other laws.

## ዘርፍ ሁለት

### ፲ የከንቲባ ጽህፈት ቤት ሥልጣንና ተግባር

ጽህፈት ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩ ል:-

፩ የከንቲባዉን ጽህፈት ቤት በበላይነት ያደራጃል፣ ይመራል፣ ያስተዳድራል፣

፪ ለካቢኔ ስብሰባ የሚቀርቡ አጀንዳዎችን አስፈላጊነት አይቶ ዉሳኔ ንዲያገኙ ያደርጋል፤ የካቢኔ ስብሰባ ቃለ-ጉባዔዎች፣ ዉሳኔዎችና ሰነዶች በሚገባ ተመዝግበዉ ንዲጠበቁ ያደርጋል፤

## ***Section Two***

### *10. Powers and Functions of Office of the Mayor*

The Office shall have the following powers and functions:-

1. superiorly organize, direct and administer Office of the Mayor;
2. cause decision be made on the importance of agenda items to be presented to the Cabinet; cause the minutes, decisions and documents of Cabinet meetings properly recorded and kept;

፫ የከንቲባዉንና የጽሕፈት ቤቱን ንቅስቃሴ የሚመለከቱ መረጃዎችን በድረ-ገጽና ሌሎች መንገዶች በማሰራጨት የሕብረተሰቡን ተሳትፎ ያረጋግጣል፤ የተለያዩ የማስተዋወቂያ መንገዶችን በማዘጋጀት የከተማዉን መልካም ገጽ ይገነባል፣

፬ ከሌሎች የዉጭ ሀገር ከተሞች፤ መንግሥ ዊና መንግሥ ዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር በጋራ ጉዳዮች የዉጭ ግንኙነት ሥራዎችን ያከናዉናል፣

፭ በመንግሥት በጀት የማይሸፈኑ ተግባሮችን ለማከናወን ወይም ማህበራዊ ችግሮችን ለመፍ ት በከንቲባዉ ፈቃድ የከንቲባዉን ስም በመጠቀም የልማት ፈንድ ያቋቁማል፣

፮ ለከተማዉ አስተዳደር ባለሥልጣናት የፕሮቶኮል አገልግሎት ይሰጣል፣ የዉጭ አገር ጉዞ ያመቻቻል፣

፯ በከንቲባዉ የሚሾሙ ወይም የሚሸለሙ ዕጩዎችን የሹመትና የሽልማት ደብዳቤ ያዘጋጃል፣ የሹመት ወይም የሽልማት ሂደቱን ያስፈጽማል፣

፰ የከተማዉን የፀጥ ሁኔ በተመለከተ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያደራጃል፣ ለከንቲባዉ ያቀርባል፣

፱ የከተማዉ አስፈጻሚ አካላትን ዕቅድ ና የዕቅዱን አፈጻጸም ይከ ተላል፣ ይገመግማል፣ ግብረ-መልስ ይሰጣል፤ ወቅ ዊ መረጃ ለከንቲባዉ ያቀርባል፣

፲ የከተማዉን ቁልፍና አበይት ሥራዎች ዓመ ዊ ዕቅድ አዘጋጅቶ ለከንቲባዉ ያቀርባል፣ የልማት ፖሊሲዎች ሥራ ላይ ንዲዉሉ ሀሳብ ያቀርባል፣

፲፩ በከንቲባዉ ሲታዘዝ የከተማዉን ብረተሰብ አቤቱ ና ቅሬ ተቀብሎ ምላሽ ይሰጣል፣

፲፪ የሠላማዊ ሠልፍ ጥያቄን ያስተናግዳል፣

፲፫ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬(፪) ድንጋጌ መሠረት ተጠሪነ ቸዉ ለከንቲባዉ የሆኑ ጽህፈት ቤቶችን ከከንቲባዉ በሚሰጥ ዉክልና መሠረት ያስተባብራል፣

፲፬ ካቢኔ ጉዳዮችን በበላይነት ይመራል።

3. ensure participation of the public by disseminating, using website and other means, information about activities of the Mayor and the office; build image of the City using different tools of promotion;
4. perform foreign relation activities on common agenda in cooperation with foreign cities, governmental and non-governmental organizations;
5. establish development fund, up on permission of the Mayor, using name of the Mayor to perform functions that would not be covered by government budget or to alleviate social problems;
6. provide protocol service and facilitate foreign travel for officials of the City Government;
7. prepare letter of appointment or award to candidates to be appointed or awarded by the Mayor; cause the award or appointment process executed;
8. gather, organize and submit to the Mayor information regarding the security condition of the City;
9. follow up, evaluate, and give feedback on the plan and performance of plan of the executive organs of the City; submit timely information to the Mayor;
10. submit to the Mayor annual plan of the key and major activities of the City; submit idea for the implementation of development policies;
11. accept and give response to the complaints and grievances of the public up on order of the Mayor;
12. handle request for peaceful demonstration;
13. corrdinate, based on delegation of the Mayor, offices accountable to the Mayor in accordance with the provisions of Article 4(2) of this Proclamation.
14. Superiorly direct cabinet affairs.

## ዘርፍ ሦስት

**፲፩ የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን**

ባለሥልጣኑ ተጠሪነቱ ለከንቲባዉ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩ ል፣

፩. በፌዴራል የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን የሚወጡ ደረጃዎችን በመከተል የከተማውን የአካባቢ ጥበቃ ደረጃዎች ያዘጋጃል፣ አካባቢ ንዳይበከል የመከላከያ ስልት ይቀይሳል፣ አግባብ ያላቸውን አካላት ከአካባቢ ጥበቃ አንፃር ያስተባብራል፣

፪. የአካባቢ ጥበቃና የተፈጥሮ ሃብት የዘለቄ አጠቃቀም ንዲኖርና ንዳይባክን ተገቢ ቅስቀሳ ያደርጋል፣ ስለ አካባቢ ጥበቃ በመገናኛ ብዙሃን ትምህርት ይሰጣል፣

፫. የኢንዱስትሪ ዝቃጭ፣ ተረፈ ምርትና ቆሻሻ በሕግ መሠረት መወገዱን ይከ ተላል፣ ይቆጣጠራል፣

፬. የአካባቢ ጥበቃ ሕጎችን መሠረት በማድረግ የማምረቻና የአገልግሎት መስጫ ተቋማት የብክለት መከላከል የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣

፭. የከርሰ ምድር ውሃ ቁፋሮና የካባ ማምረት ሥራ ለሚያካሂዱ የሙያ ፈቃድ ይሰጣል፣ ቁጥጥር ያደርጋል፣

፮. ከሚመለከ ቸው አካላት ጋር በመመካከር የአካባቢ ጥበቃ ሥልቶችን አዘጋጅቶ ያቀርባል፤ ሲፀድቁም ተግባራዊ መሆናቸውን ያረጋግጣል፣

፯. የተለያዩ ዕፅዋት የሚተከሉበትን ቦ ና የሚሰጡትን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ባህላዊና አካባቢያዊ ጠቀሜ በማጥናት ተግባራዊ ንዲሆኑ ያደርጋል፤ በከተማው መሪ ኘላን ለመናፈሻ፣ ለደን፣ ለወንዝ ዳርቻና ለሌላ አረንጓዴ ቦ ልማት በተከለሉ ቦ ዎች ላይ የሚተከሉትን ዕፅዋት አይነት በሚመለከት ያማክራል፤ ያስተዋዉቃል፣

## Section Three

**11. Environmental Protection Authority**

The Authority, being accountable to the Mayor, shall have the following powers and functions:

1. prepare the City's environmental protection standards in accordance with the standards prepared by the Federal Environmetal Protection Authority; design strategies to protect the environment from pollutions; coordinate stakeholders with regards to environmental protection;
2. cause the due propagation of environmental protection and the sustainable and non-abuse use of natural resources; aware the public about environmental protection through mass media;
3. follow up and control that the disposition of industrial residue, by-products and waste are in accordance with the law;
4. issue in accordance with the environmental laws certificate of competence of pollution prevention for production and service rendering institutions;
5. issue professional license and supervise those engaged in the drilling of underground water and quarries;
6. in consultation with the concerned bodies, prepare and submit strategies of environmental protection;ensure implementation of same upon approval;
7. study the site and economic, social, cultural and environmental benefits of various plant species and implement same; determine the plant type and quantity to be planted on areas designated for recreational parks, forest, beaches and other green areas in accordance with the master plan of the City;

፰ በከተማው ውስጥ የበለጠ ውጤ ማ በመሆናቸው መልማት ያለባቸው የውጭና አገር በቀል የዕፅዋት ዝርያዎችን በማጥናት የሚለሙበትን አግባብ ያስተዋዉቃል፣ በከተማው ውስጥ ያልተሞከሩና የማይ ወቁ የዕፅዋት ዝርያዎች ከውጭ አገር አምጥተው በከተማው ክልል ውስጥ ማልማት ለሚፈልጉ ሰዎች ፈቃድ ይሰጣል፣

፱ በከተማው መሪ ኘላን ለአረንጓዴ በ ልማት በተከለሉ የደንና የወንዝ ዳርቻ ቦ ዎች ላይ ደን ንዲለማና የአፈርና ውሀ ጥበቃ ሥራዎች ንዲከናወኑ ያደርጋል፤ የሚመለከ ቸውን አካላትና የከተማውን ነዋሪዎች በማስተባበር የደን ቦ ዎችና የወንዝ ዳርቻዎች በተመረጡ የዕፅዋት ዝርያዎች የሚለሙበትን ስልት ይቀይሳል፣ አስፈላጊውን ገዛ ያደርጋል፣

፲ በአስተዳደሩ ይዞ ስር የሚገኙ ጥብቅ ደኖች በሥርዓት መጠበቃቸዉን ያረጋግጣል፤ መቆረጥ ለሚገባቸዉ ፈቃድ ይሰጣል፤ በሥርዓት መቆረጣቸዉንም ይቆጣጠራል፤ ተከ ይነት ያለው የሙያ ድጋፍና የግንዛቤ ማሳደጊያ ትምህርት ይሰጣል፤ ለደንና ለወንዝ ዳርቻ ሥፍራነት መዋል የሚገባቸው ተጨማሪ ቦ ዎችን በማጥናት ያቀርባል፣ ሲወሰንም ንዲለሙ ያደርጋል፣

፲፩ የደን ቦ ዎች፣ የወንዝ ዳርቻዎች፣ የጋራ መገልገያ አረንጓዴ ቦታዎች ለታለመላቸዉ ዓላማ መዋላቸዉን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ የሚዉሉበትንም ስልት ያስተዋዉቃል፣ ያማክራል፤

፲፪. በመንግስትም ሆነ በግል የይዞ ክልል የለሙ ዛፎችን ለመቁረጥ ሲፈለግ ፈቃድ ይሰጣል፣ ከባለስልጣኑ ዕውቅናና ፈቃድ ውጭ ንዳይቆረጡ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል።

## ዘርፍ አራት

### ፲፪ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ

፩ ኤጀንሲዉ ተጠሪነቱ ለከተማዉ ከንቲባ ሆኖ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፲፩/፪ሺ፩ የተደነገጉ ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩ ል።

8. study and promote the plantation site for plants of local and foreign origin proved to be more effective; give license to persons who want to import and grow plant species not known and tried in the City;
9. cause the undertaking of forest development and soil conservation activities on forest areas and beaches designated as green areas in accordance with the master plan of the City; in collaboration with concerned organs and residents of the City, design strategy and give support for growing selected species of trees on same;
10. ensure that reserved forest areas under the holding of the City Government are properly preserved; give professional support and awareness education on continued basis; study and present additional sites that can be used as beach and forest areas; initiate the development thereof;
11. follow up and control that forest areas, beaches, green areas for public use are serving the purpose sought; promote and advise on techniques by which they serve same;
12. give permit for cutting of trees grown on private or Government holdings; follow up and supervise to protect the cutting of trees without the knowledge and permit of the Authority.

## Section Four

### 12. Technical and Vocational Education and Training Agency

1. The Agency, being accountable to the Mayor, shall have powers and functions provided by Proclamation No. 11/2009 of the Addis Ababa City.

፪ የ ንጦጦ፤ የጀኔራል ዊንጌት፤ የአዲስ አበባ ተግባረዕድ፤ የንፋስ ስልክ፤ የምሥራቅ፤ የአቃቂ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጆች ተጠሪነት ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ ሆኖ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጆች ንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፲፪/፪ሺ፩ የተደነገገው ስልጣንና ተግባር፣ ንዲሁም አደረጃጀትና አሰራር ይኖራቸዋል።

## ዘርፍ አምስት

### ፲፫ የገቢዎች ባለሥልጣን

፩ የከተማዉን ገቢዎች ባለሥልጣንን ተግባራት በሙሉ ወይም በከፊል የከተማዉ አስተዳደር አግባብነት ላለዉ የፌደራል መንግሥት አካል በዉክልና መስጠት ይችላል፣

፪ ባለሥልጣኑ ተጠሪነቱ ለከንቲባዉ ሆኖ ሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

ሀ የገቢ አወሳሰንና የገቢ ሂሳብ አያያዝ በተሳለጠና ብቃት ባለዉ መልኩ ለማከናወን የሚያስችሉ የአሠራር ዘዴዎችን ይቀይሳል፣ ተግባራዊነታቸዉን ይከታተላል፤

ለ አዳዲስ የገቢ ምንጮችን እያጠና በማቅረብ በሚፈቀደዉም መሠረት በሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፣

ሐ ግብር ከፋዮችን ለይቶ ለማወቅና ለመመዝገብ የሚያስችሉ አሠራሮችን ተግባራዊ ያደርጋል፤ በከተማው የሚሰበሰቡ ገቢዎችን ይወስናል፣ የግብር ውሳኔዎችን ለግብር ከፋዮች በጽሑፍ ያስ ዉቃል፣ ይሰበስባል፤

መ በከተማ፣ በክፍለ ከተማዎችና በወረዳዎች የተሰበሰቡ ገቢዎች በፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ የሚተዳደር የከተማ አስተዳደሩ ግምጃ ቤት በወቅቱ ፈሰስ መደረጋቸውን ያረጋግጣል፤

2. The Entoto, General Winget, Addis Ababa Tegbareid, Nefas Silk, Misrak, and Akaki Technical and Vocational Education and Training Colleges shall be accountable to the Technical and Vocational Education and Training Agency; they shall have the powers and functions, the organizational structure and procedures provided by the Addis Ababa City Technical and Vocational Education and Training Colleges Re-establishment Proclamation No 12/2009.

## Section Five

### 13. Revenue Authority

1. The City Government may delegate the powers and functions of the Authority fully or partially to the appropriate Federal Government body;
2. The Authority, being accountable to the Mayor, shall have the following powers and functions:-
   a. set up systems for efficient and effective determination of revenue and keeping of revenue books of account, follow up implementation of same.
   b. undertake studies and recommend new sources of revenue and follow up the implementation of same upon approval;
   c. implement mechanisms for identification and registration of tax payers; assess the revenues collected in the City; notify to the tax payers the assessment of taxes in writing and collect same;
   d. ensure the duly deposition of revenues collected by the City, Sub-Cities and Weredas in the treasury of the City Government administered by the Finance and Economic Development Bureau;

ሠ ግብር ከፋዮች ሕጎችን አውቀው መብትና ግዴ ቸውን ንዲወጡ ይቀሰቅሳል፤ ግብር የመክፈል ግዴ ቸውን በሕግ መሠረት መወጣ ቸውን ያረጋግጣል፣

ረ የገቢ ግብር ዕዳ ስረዛ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለካቢኔ አቅርቦ ያሰርዛል::

## ዘርፍ ስድስት

**፲፬. የአዲስ አበባ ስፖርት ኮሚሽን**

ኮሚሽኑ ተጠሪነቱ ለከተማዉ ከንቲባ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

፩ የአራት ኪሎ፣ የራስ ይሉና፣ የጃንሜዳ ስፖርት ትምህርትና ሥልጠና ማዕከላትን ንዲሁም የአበበ ቢቂላን ስ ዲየም በበላይነት ያስተዳድራል፤ የሚመሩባቸውን የአሠራር መመሪያዎች በማውጣት ተግባራዊ ያደርጋል፣ የሰው ይል መዋቅር አጥንቶ ሲፈቀድ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፪ የከተማው ነዋሪ በስፖርት ለሁሉምና በባህላዊ ስፖርት ተሣታፊና ተጠቃሚ የሚሆንበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

፫ በከተማው በስፖርት የሠለጠነ የሰው ኃይል ለማፍራት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ይሰራል፤

፬ በከተማው አስተዳደር ክልል የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎችንና የስፖርት ማበልፀጊያ ማዕከላት እንዲስፋፉ ያደርጋል፤

፭ በከተማው አስተዳደር ለስፖርት ተግባራት የሚውሉ የስፖርት ትጥቆችና መሣሪያዎች አቅርቦት የሚሟላበትን ሁኔታ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ያመቻቻል፤

፮ በፌዴራል መንግሥቱ የሚመለከተው አካል በሚወሰነው መሠረት የስፖርት ህክምና አገልግሎት መደራጀቱን፣ በስፖርት አበረታች መድሃኒቶችና ዕፆች መጠቀምን ለመከላከል የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋቱን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፤

e. propagate with a view to creating awareness among the tax payers in order that they may fulfill their obligation; ensure that they have fulfilled their obligation of paying taxes in accordance with the law;

f. where a need arises thereof, submit to the Cabinet for cancellation of debt of income tax.

## Section Six

**14. Addis Ababa Sport Commission**

The Commission, being accountable to the Mayor, shall have the following powers and functions:-

1. superiorly administer the Arat Kilo, Ras Hailu, Jan Meda sport Education and Training Centers and Abebe Bikila Stadium; issue directives on working procedures and implement the same; implement upon approval their human resource structure;
2. facilitate conditions whereby the residents of the City participate in and benefit from sport for all and traditional sports;
3. work with the concerned bodies to produce trained manpower in the field of sport within the City;
4. cause the expansion of sport facilities and centers within the boundary of the City Government;
5. facilitate the supply of adequate sportswear and equipment used for sports activities within the City Government in cooperation with the concerned bodies;
6. ensure and follow up the organization of sport medical facilities in accordance with the decision of the concerned Federal Government body; and the adoption of systems for controlling doping practices;

፯. በፌዴራል መንግሥቱ የሚመለከተው አካል የሚወጣው እንደተጠበቀ ሆኖ በከተማው አስተዳደር የስፖርት ማህበራት ስለሚቋቋሙበት ሁኔታ መመሪያ ያወጣል፣

፰. በከተማው አስተዳደር የሚቋቋሙ የስፖርት ማህበራትን ይመዘግባል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤

፱. በከተማው ደረጃ የስፖርት ልማት ፈንድ የሚቋቋምበትን ስልት ይቀይሳል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፲. በከተማው ውስጥ የስፖርት ውድድሮች ሲዘጋጁና ሲካሄዱ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤ ከሌሎች እህት ከተሞች ጋር ስፖርትን በሚመለከት ዉድድር፣ የልምድ ልዉዉጥና ትብብር ያደርጋል፤

፲፩. የስፖርት ትምህርት፣ ሥልጠናና የምርምር ተቋሞች የሚቋቋሙበትን ስልት በመቀየስ በሚመለከተዉ አካል ሲጸድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፣

፲፪. በሳይንሳዊ ጥናት ላይ የተመሠረቱ የአካል ብቃት ማሠልጠኛ ዘዴዎች በማዘጋጀት ስፖርተኞች፣ አሠልጣኞች፣ የስፖርት ዳኞችና የመሳሰሉት እንዲሰለጥኑ ያደርጋል፣

፲፫. ከሚመለከታቸው የአስተዳደሩና የፌዴራል አካላት ጋር በመተባበር የከተማውን ነዋሪዎች የስፖርት ተሳትፎ ለማጎልበት በጋራ ያቅዳል፣ የአስተዳደሩን የስፖርት ውድድሮች ያዘጋጃል፣ ይመራል፣ በተለይም ከአስተዳደሩ ትምህርት ቢሮ ጋር በመተባበር የትምህርት ቤቶች የስፖርት ውድድር እንዲስፋፋና እንዲጠናከር ያደርጋል፣

፲፬. በአገር አቀፍ ፖሊሲና በሕግ መሠረት የስፖርት ማህበራትንና የስፖርት ክለቦችን ይመዘግባል፣ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ የስፖርት ማህበራት በስፖር ዊ ንግድ ሥራዎች ንዲሳተፉ ያበረ ል፣

፲፭. በከተማው ውስጥ የስፖርት ማህበራትና ክለቦች ስለሚቋቋሙበትና ስለስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራ አጠቃቀምና አሠራር መመሪያ ያወጣል፣

7. without prejudice to that issued by the concerned body of the Federal Government, issue directives governing the establishment of sports associations;
8. register and support associations operating within the City Government;
9. devise mechanisms for the establishment of sports development fund at the City level, and implement same upon approval;
10. Provide necessary support in organizing and conducting sport games within the City; enter into competition, share experience and cooperate with other sister cities;
11. devise strategy for the establishment of sport educational, training and research institutions; implement same upon approval by the concerned body;
12. train sports persons, trainers, arbitrators and the like by developing scientific physical training methods;
13. in collaboration with the concerned organs of the City and the Federal Governments, prepare joint plans for enhancing participation of residents in sports; organize and direct the City's sports competition; particularly, promote and strengthen sports competitions in the schools of the City in collaboration with Education Bureau;
14. register sport associations and clubs; provide certificate of registration in accordance with the law and national policy; encourage that sport associations involve in sport related commercial activities;
15. issue directive on the establishment of sport associations and clubs and on the use and procedure of sporting areas;

፲፮ በሕግና በሀገር አቀፍ ፖሊሲ መሠረት የስፖርት ማኅበራትንና የስፖርት ክለቦች፣ ንዲሁም ጅምናዚየሞች ይመዘግባል፣ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ የሙያ የስራ ፍቃድ ይሰጣል፤ በውጭ ኦዲተር የተመረመረ የሂሳብ ሪፖርት ከየማህበሩ እንዲቀርብለት በማድረግ የስፖርት ማኀበራት ገቢ ለዓላማቸው ብቻ መዋሉን ያረጋግጣል፣

፲፯ የአስተዳደሩ ስፖርት ምክር ቤት በየደረጃው በማቋቋም በፌዴራል መንግስት የስፖርት ፖሊሲና ህግ መሠረት የስፖርት ምክር ቤቱን አደረጃጀት ያጠናክራል፣ ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣

፲፰ ከሚመለከተዉ አካል ጋር በመተባበር የሴቶችና የአካል ጉዳተኞች የስፖርት ተሳትፎና ተጠቃሚነት የሚጎለብትበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

፲፱ ዓላማውን ለማስፈፀም የሚረዳ በክፍለ ከተማ ደረጃ ተጠሪነቱ ለክፍለ ከተማዉ ዋና ሥራ አስፈጻሚ የሆነ ጽህፈት ቤት እንዲሁም በወረዳ ደረጃ ተጠሪነቱ ለወረዳዉ ዋና ሥራ አስፈጻሚ የሆነ ጽህፈት ቤት ያደራጃል፣ ይመራል፡፡

16.register sport associations, clubs and gymnasiums; provide certificate of registration in accordance with the law and national policy; issue certificate of competency; cause inspection of their books of account by external auditors and ensure that the sport associations use their income only for the desired goal;

17. establish the sports council of the City's Government at various levels and in accordance with the Federal Government sport policy and law, strengthen, direct and supervise the structure of the council;

18. facilitate conditions, in coordination with the concerned body, for the women and persons with disability to participate in and benefit from sport;

19. establish and direct sport Office at Sub-city level which is accountable to the Chief Executive of the Sub-city and sport office at Wereda level which is accountable to the Wereda Chief Executive as are appropriate to the attainment of its objectives.

## ***ዘርፍ ሰባት***
## ***የአቅም ግንባ ቢሮ ና በሥሩ ያሉ አስፈጻሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር***

**፲፭. የአቅም ግንባ ቢሮ**

የአቅም ግንባ ቢሮ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩ ል፡-

፩ የሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲን፣ የአዲስ አበባ ከተማ ሥራ አመራር ኢንስቲትዩትንና፣ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ልማት ኤጀንሲን በበላይነት ያስተባብራል፣ ይመራል፣

፪ የአቅም መገንቢያ አቅሞች ንዲፈጠሩና ንዲጠናከሩ ያደርጋል፣ በአስተዳደሩ አስፈጻሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት ንዲሁም በሌሎች የአስተዳደሩ አካላት፣ በብዙሃን ማኀበራትና በግል ባለሀብቶች ሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

## ***Section Seven***
## ***Powers and Functions of the Bureau of Capacity Building and Executive Organs accountable to it***

**15. Bureau of Capacity Building**

The Bureau shall have the following powers and functions:-

1. coordinate and direct the Civil Service Agency, Addis Ababa City Management Institute, and Information Communication Technology Development Agency;
2. cause the establishment and strengthening of capacity for capacity building; ensure the implementation of same by the various executive organs, the municipal organs, and also other organs of the Government, mass organizations and the private sector;

፫ የአስተዳደሩ አስፈጻሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት ብቃት ያለው የሥራ አመራር የሚከተሉበትንና የተሻለ አገልግሎት ለመስጠት የሚችሉበትን ስልት ይቀይሳል፤

፬ የአስተዳደሩን የአቅም ግንባ ፕሮግራሞችና ሥራዎች በበላይነት ያስተባብራል፣ ይመራል፣ ያስፈፅማል፣ አስፈላጊውን የቴክኒክና የሙያ ድጋፍ ይሰጣል፤

፭ ለአቅም ግንባ አስፈላጊ የሆኑ ተቋማት ንዲስፋፉ ያደርጋል፣ የአስተዳደሩን የኢንፎርሚሽንና ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ስራዎችን በበላይነት ያስተባብራል፣ ይመራል፤

፮ በአስተዳደሩ ውስጥ የሰለጠነ የሰው ይል አስተዳደር፣ አደረጃጀትና አሰራር ተግባራዊ ለማድረግ የሚቻልበትን ስልት በመቀየስ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ መሆኑን ያረጋግጣል፣

፯ የአስተዳደሩ አካላት የተሻለ አገልግሎት አሰጣጥ እንዲኖራቸዉ የሚያስችል የክትትል፣ ድጋፍና ምዘና ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል።

3. design strategies for executive and municipal organs to have an effective management and to render better services;

4. coordinate, direct, and implement capacity building programs and activities of the Government and provide the necessary technical and expertise supports;

5. initiate the expansion of institutions required for capacity building; coordinate and direct the information and communication technology activities of the Government;

6. design and submit strategy for implementation of qualified human resource management and administration system; ensure implementation of same upon approval;

7. install and follow up a system of follow up, support and evaluation with the view to enable the Government organs have better service delivery.

## ፲፮. የሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ

ኤጀንሲዉ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩ ል፤

፩ ለመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሚያስፈልጉ የሥራ መደቦች የሚመደቡባቸውን ክፍል ሥራዎችና ደረጃዎች ንዲሁም ለ ያንዳንዱ ክፍለ ሥራ የሚጠየቀውን ተፈላጊ ችሎ በሀገር አቀፍ ደረጃ በወጡ የትምህርት፣ የሥልጠናና የልምድ አጠቃላይ መመዘኛዎች መሠረት በማድረግ ይወስናል፤

፪ ለመንግሥት ሠራተኞች የተፈቀደው ደመወዝ፣ የልዩ ልዩ አበሎች ክፍያ፣ የጥቅማ ጥቅምና ሌሎች የሥራ ሁኔ ዎች የአስተዳደሩን የመንግሥት ሠራተኞች በሚመለከት በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፣ በ ነዚህ ጉዳዮች አፈጻጸም የሚቀርቡ አቤቱ ዎች በመመርመር ተገቢውን ይወስናል፤

## 16. Civil Service Agency

The Agency shall have the following powers and functions:

1. determine the class of positions and grades to which all positions, in government offices, shall be assigned as well as the required qualification for each class of positions in accordance with the generally established requirements for education, training and experience at the national level;

2. ensure that salary, payment of various allowances, benefits and other working conditions in relation to civil servants of the City Government are implemented; render decisions for petitions related to these matters;

፫ በከተማው አስተዳደር የሲቪል ሰርቪስ ሕግ መሠረት የአስተዳደሩ የመንግሥት ሠራተኞች የሥራ አፈጻጸም መመዘኛና ሌሎች መመሪያዎችን ያወጣል፣ በሥራ ላይ መዋላቸውን ይቆጣጠራል፤

፬ የአስተዳደሩ የመንግሥት ሠራተኞች አቆጣጠር፣ አመዳደብ፣ የደረጃ ዕድገት፣ የደመወዝ ስኬል፣ ዝውውር፣ ሥልጠናና የዲሲኘሊን አጠባበቅ በሕግ መሠረት መፈጸሙን ይቆጣጠራል፣ በሕግ አተረጓጎምና አፈጻጸም ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በማጥናትና መፍትሄ በማፈላለግ ተግባራዊ ያደርጋል፣

፭ የከተማ አስተዳደሩ የመንግሥት ሠራተኛን በችሎ ማነስ ምክንያት ከሥራ ለማሰናበት የሚቀርብ ጥያቄ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፤ በሕግ መሠረት የአስተዳደሩ የመንግሥት ሠራተኞች ከጡረ ዕድሜ ክልል በላይ አገልግሎ ቸው ንዲራዘም በሚቀርቡ ጥያቄዎች ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፣

፮ የአስተዳደሩ የሲቪል ሰርቪስ የሰው ይል በዝርዝር በመለየት ይመዘግባል፤

፯ የሲቪል ሠርቪስን በተመለከተ የወጡ ፖሊሲዎች፣ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መተግበራቸውን ይቆጣጠራል::

## ፲፯. የአዲስ አበባ ከተማ ሥራ አመራር ኢንስቲትዩት

፩ የከተማው ሥራ አመራር ኢንስቲትዩት ተጠሪነቱ ለአቅም ግንባ ቢሮ ሆኖ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥራ አመራር ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፲፫/፲፱፻፺፩ የተመለከቱት ሥልጣንና ተግባራት ንዲሁም አደረጃጀትና አሠራር ይኖረዋል፤

፪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ የከተማው ስራ አመራር ኢንስቲትዩት በቦርድ ይመራል፣ የቦርዱ ስልጣንና ተግባር ንዲሁም አደረጃጀትና አሰራር በከተማው ካቢኔ በሚወጣ ደንብ ይወሰናል::

3. in accordance with the civil servants law of the City Government, issue standards of performance appraisal of the city civil servants and other directives; supervise the implementation of same;

4. supervises the execution of recruitment, placement, promotion, salary scale, transfer, training and compliance to disciplinary rules of the civil servants in the City Government is in accordance with the law; undertake studies in search of solutions for the difficulties raised with regard to interpretation and application of the laws and cause the implementation of same.

5. give final decisions upon request submitted for employment termination of civil servants of the City Government on grounds of inefficiency and on extension of the civil servants of the City Government beyond the retirement age in accordance with the law;

6. register the human resource in the City Government civil service upon identifying the details.

7. control the implementation of policies, proclamations, regulations and directives issued in relation to the civil service.

## 17. Addis Ababa City Urban Management Institute

1. The Institute shall have the powers and functions as well as organizational structure and operation as defined in the Addis Ababa City Management Institute Establishment Regulations No 13 / 1999;
2. Notwithstanding the provisions stated in Sub-Article (1) of this Article, the Urban Management Institute shall be directed by board; powers and functions of the board as well as organizational structure and functions shall be determined by regulation issued by the City Cabinet.

፲፰ የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ልማት ኤጀንሲ

፩ ኤጀንሲው በፌዴራሉ ኤጀንሲ አስተባባሪነት ኢንፎርሜሽንና ኮሚኒኬሽንን በሚመለከት ለሀገራዊ አገልግሎት እንዲውሉ ተዘጋጅተው የጸደቁትን መመሪያዎች፣ ደንቦች፣ ሌሎች ሕጎችና ቅንጅ ዊ የአሠራር ሂደቶችን በመከተል የሚጠበቅበትን ሓፊነት መወጣቱ እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩ ል፡-

፪ በፌዴራል መንግሥት የወጡ የኢንፎሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ልማት ፖሊሲዎችና ሕጎች በከተማው አስተዳደር ውስጥ እንደየአግባቡ በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፣

፫ ከፌዴራል መንግሥት የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ልማት ፖሊሲና ሕግ ጋር የሚጣጣም የአስተዳደሩን ፖሊሲና ሕግ ያመነጫል፤ ፖሊሲውን በብቃት ለማስፈጸም የሚያስችል አቅም በከተማው አስተዳደር መሥሪያ ቤቶች እንዲገነባ አግባብነት ያለው ስልት ያዘጋጃል፤ ሲፈቀድም ተግባራዊነቱን ያረጋግጣል፤ አፈጻጸማቸውን የሚያሳኩ መመሪያዎችን ያወጣል፤

፬ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ልማትን አስመልክቶ ተገቢውን የከተማውን አስተዳደር መረጃ መከ ተል፣ ማሰባሰብና መተንተን የሚያስችል ሥርዓትና ከተማ አቀፍ አቅምን ይገነባል፤ የፌዴራል ኤጀንሲውን መመዘኛ መስፈርቶች በመከተል ደረጃ አውጥቶ ወይም በወጣው ደረጃ መሠረት ሃርድዌርና ሶፍትዌር ያዘጋጀ ለአስተዳደሩ መስሪያ ቤቶች ያቀርባል፤ ተግባራዊ መሆኑን ይከ ተላል፤ በዚህ መልኩ ለሚያዘጋጃቸው የኢንፎርሜሽንና ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂዎች ስም ይሰጣል፣ ከኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ልማትና አጠቃቀም ጋር በተያያዘ የአስተዳደሩን መሥሪያ ቤቶች ያማክራል፣

**18. Information Communication Technology Development Agency**

1. Notwithstanding that it discharges the respective responsibilities in accordance with the laws, regulations, directives and procedures of integrated performance in relation to information and communication issued, under the coordination of the Federal Agency, for national use, the Agency shall have the following powers and functions:-
2. ensure the policies and laws of information communication technology, issued by the Federal Government, *mutatis mutandis* implemented in the City.
3. initiate policy and law of the City that is in line with the Federal Government information communication development policy and law; devise appropriate technique to build capacity for the efficient implementation of the policy in the offices of the city government; ensure the implementation of the same upon approval; issue directives for implementation of the policy;
4. build city-wide capacity enabling follow up, gather and describe proper information of the City in relation to information communication technology; prepare and provide hardware and software to the offices of the City Government, by setting levels or following the levels already set, based on standard requirements of the Federal Agency; follow up its application; issue name to information and communication technologies it prepared in this way; advise offices of the City Government on matters related to information communication technology;

፭ ከሚመለከ ቸው አካላት ጋር በመተባበር በከተማው ውስጥ በሚገኙ የአስተዳደሩ ትምህርት ቤቶች፣ የኮምፒውተር መረብ ዝርጋ ሥራዎች መሠራ ቸውን ያረጋግጣል፤ ተገቢውን ቴክኒካዊ ድጋፍ ያደርጋል፤

፮ በሥራ ላይ የሚገኙትንና ወደፊትም በሥራ ላይ የሚውሉ የከተማው አስተዳደር መሥሪያ ቤቶች የኮምፒውተር መረቦችና አፕሊኬሽኖች ከቴክኒክና አሠራር አኳያ መቀናጀትና መናበብ መቻላቸውን ያረጋግጣል፤

፯ ለከተማው ነዋሪዎች አገልግሎት በመስጠት ላይ ያተኮሩ የከተማው አስተዳደር መሥሪያ ቤቶች መሠረ ዊ ሲስተሞችና አገልግሎቶች በኮምፒውተር የተደገፉ ንዲሆኑና ደረጃ በደረጃም ለተጠቃሚዎች በቀጥ አገልግሎት ሲሰጡ በሚችሉበት ሁኔ መመቻቸ ቸውን ያረጋግጣል፤

፰ የፌደራሉ ኤጀንሲ በሚያወጣው መመሪያ ወይም በሚሰጠው ምክር መሠረት በከተማው አስተዳደር መሥሪያ ቤቶች ውስጥ የተቀናጀ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ልማትን ጥቅም ላይ ለማዋል የሚደረግ ሂደትን ለማፋጠን የሚያስችል የሥልጠና፣ የፕሮጀክት አስተዳደርና አፈጻጸም ድጋፍ ያደርጋል፤

፱ የፌደራሉ ኤጀንሲ በሚያወጣው አንድ ወጥ የአሰራር ስ ንዳርድ መሠረት የከተማውን አስተዳደር መረጃ ይሰበስባል፤ያከማቻል፣ያጠናቅራል፣ ይተነትናል፣ያሰራጫል፤ ንዲሁም ጥራቱ፣ ደ ንነቱና አስተማማኝነቱ ንዲጠበቅ ያደርጋል፤

፲ በከተማው አስተዳደር ውስጥ የመጀመሪያ ደረጃ ዳ አሰባሰብ አተናተንና ሥርጭትን የሚያግዝ የአሠራር ሥርዓት ንዲኖር ያደርጋል፤

፲፩ በኢንፎሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ አማካኝነት ከሚገኙ የመረጃ ምርቶች፣ አገልግሎቶችና አጠቃቀማቸው ጋር የተያያዙ ተግባራትን በከተማው አስተዳደር ውስጥ ለማፋጠንና ለማቀላጠፍ የሚያስችሉ ሥራዎችን በህግ መሠረት ያከናውናል፤

5. ensure, in cooperation with the concerned bodies, the installation of computer network in the schools within the City Government; provide the necessary technical support;
6. ensure the integration and readability of computer networks and applications of offices of the City Government that are currently functional as well as those which will be functional in the future;
7. ensure that the basic systems and services of offices focusing on rendering service to the residents of the City are supported by computer and facilitated in a way to provide, step by step, direct service to the customers;
8. provide, based on directive issued or advice given by the Federal Agency, training, project management and implementation support with the view of facilitating the process of making use of information communication technology in the offices of the City Government;
9. based on work standard issued by the Federal Agency, gather, deposit, analyse, interprate and disseminate information of the City Government; cause the quality, security and reliability of the information maintained;
10. cause existence of a system supporting primary level data collection, interpretation, and dissemination in the City Government;
11. perform, in accordance with law, activities related to products of information, services and their use resulting from information communication technology that enable expediency and fastness of same within the City Government;

፲፪ በከተማው አስተዳደር ውስጥ የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ባለሙያ በዓይነት በብዛትና በጥራት ለማፍራት ከሚመለከ ቸው የትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ጋር ተባብሮ ይሠራል፤ የኢንፎሜሽንና ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂን መጠቀም ንዲሁም የተዘረጋውን ሲስተም ያለችግር ማሠራት የሚችልና የሚጠግን የሰው ይልን የማሠልጠን ሥራ ይሠራል፤

፲፫ የከተማውን አስተዳደር ልማት ለማፋጠን የኢንፎሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ በከተማው አስተዳደር የኢኮኖሚ ዘርፍ የልማት ፕሮግራም ውስጥ ተገቢውን ሚና ንዲጫወት ያደርጋል፤

፲፬ የኢንፎርሜሽንና ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ልማት ወደ ከተማው ነዋሪ ብረተሰብ ሰርጾ ጥቅም ንዲሰጥ በየደረጃው የማስተዋወቅ ሥራ ይሰራል፤ የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ወደ ከተማው ነዋሪ ብረተሰብ በማስረጽ ላይ የሚያተኩሩ የምርምርና የልማት ሥራዎችን ያስተባብራል፤ ድጋፍ ይሰጣል፤

፲፭ በኢንፎርሜሽንና ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ከተማ አቀፍ ልማት ጥረት ውስጥ የግል ክፍለ ኢኮኖሚውን ተሳትፎ ለማጎልበት የሚያስችሉ የፕሮጀክት ሀሳቦችን ያመነጫል ያዘጋጃል፤

፲፮ ከተማ አቀፍ የኢንፎርሜሽንና ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ልማትን በማስረጽ ውጤ ማ አስተዋጽኦ ለሚያስመዘግቡ ተቋማትና ባለሙያዎች ሽልማት ይሰጣል፤ በሂደቱም በከተማው አስተዳደር ውስጥ ቴክኖሎጂዎችን የማስተዋወቅ ዝግጅቶችን ያስተባብራል፤

፲፯ በከተማው ውስጥ የኮምፒዉተር መረብ ዝርጋ ስራዎችን ለመስራት ለሚፈልጉ አካላት በጥናት ላይ የተመሠረተ ፈቃድ ይሰጣል፤

፲፰ የፌዴራሉ ኤጀንሲ በየጊዜው በሚያዘጋጃቸው መመዘኛ መስፈርቶች መሠረት በከተማው አስተዳደር ውስጥ የኢንፎሜሽንና ኮሚኒኬሽን ተክኖሎጂን ድገትና የውጤቱን ደረጃ ለመለካት የሚያስችሉ ዳ ዎችን ይሰበስባል፤ ይተነትናል፤

12. work in cooperation with the concerned educational and training institutions towards producing qualified information communication technology personnel in diversity, quantity and quality within the City Government; perform the task of training persons operating and maintaining the installed system of information and communication technology;

13. cause information communication technology play proper role in the economic sector development program of the City Government so that enhance development of the City Government.

14. perform the task of promoting at different levels information and communication technology development so that it becomes useful being deep rooted within the residents of the City; coordinate and provide support to research and development activities focusing on inculcating information communication technology within the residents of the City.

15. initiate and prepare project ideas that can enable strengthening participation of the private sector in the effort of city-wide information and communication technology development.

16. offer award to institutions and professionals that have effective contribution in the effort of diffusing citywide information and communication technology development; in the process coordinate programs of introducing technologies in the city administration.

17. issue license based on study to those who intend to involve in computer network installation activity in the City.

18. gather and interprete data, based on standard requirements issued from time to time by the Federal Agency, that can enable measure the developement and the level of result of information and communication technology in the City Government.

## ዘርፍ ስምንት
## የትምህርት ቢሮና የሚያስተባብረው ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ስልጣንና ተግባር

**፲፱. የትምህርት ቢሮ**

ቢሮዉ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩ ል:-

፩ የኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅን በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል::

፪ የሀገሪቱን የትምህርት ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና ደረጃ በመጠበቅ የከተማውን አስተዳደር ተጨባጭ ሁኔ በማገናዘብ የመጀመሪያ ደረጃ ሥርዓተ ትምህርት ያዘጋጃል፣ መጽሐፍት ያሳትማል፣ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች መሟላ ቸውን ያረጋግጣል፣ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚወጣውን መስፈርት መሠረት በማድረግ በከተማው ውስጥ የሚሰሩትን የትምህርት ቤቶች ደረጃ ያዘጋጃል፣ ሲጸድቅም ተግባራዊ መሆኑን ያረጋግጣል::

፫ በከተማው ውስጥ አገር አቀፍ ፈተናዎችን ያስፈጽማል፣ በከተማው ወስጥ በሚገኙ የመጀመሪያና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተዘጋጅተው የሚሰጡ ፈተናዎችንና የምስክር ወረቀቶችን ብቃት የሚወስን ደረጃ ያዘጋጃል፣ ሲጸድቅም ሥራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፤

፬ ከተማ አቀፍ የሆኑ ፈተናዎችን ያዘጋጃል፤ ያስፈጽማል

፭ በመገናኛ ዘዴዎች የተደገፉ የትምህርት ኘሮግራሞች ንዲሰጡ ያደርጋል፣ የተከ ይ ና የርቀት ትምህርት ኘሮግራሞች የሚስፋፉበትን ሁኔ ይቀይሳል፣ ተግባራዊነቱንም ይከ ተላል፣ ይቆጣጠራል፤

፮ ለሴቶች፣ ለሕፃናት፣ ለጎልማሶችና ልዩ የትምህርት ፍላጎት ላላቸው ሌሎች ሰዎች ለሚሰጡ የትምህርት አገልግሎቶች ልዩ ድጋፍ ንዲሰጥ ያደርጋል፤

፯ በሀገር አቀፍ ደረጃ በሚወጡ የብቃት መመዘኛዎች መሠረት መምህራን ና ሌሎች የትምህርት ባለሙያዎችን ያሰለጥናል ወይም ንዲሰለጥኑ ያደርጋል፣ ንዲሁም ለክፍለ ከተማ የትምህርት ጽህፈት ቤቶችና በትምህርት ዘርፍ ለተሰማሩ ሌሎች አካላት ተቋማዊና ቴክኒካዊ ድጋፍ ይሰጣል፤

## Section Eight
## Powers and Functions of Education Bureau and the Higher Education Institutions it coordinates

**19. Education Bureau**

The Bureau shall have the following powers and functions to:

1. direct and coordinate the Kotobe College of Teachers Education,
2. prepare elementary level curriculum, publish books and ensure the availability of teaching aid materials in compliance with the national education policy, strategy and standard and in consideration of the prevailing situation of the City Government; Prepare standard for the construction of schools in the City in accordance with the national requirements and implement same upon approval.
3. execute national examination in the City; prepare standards for examinations and certificates given by elementary and high schools found in the City; ensure implementation of same upon approval;
4. prepare and administer City-wide exams;
5. cause the provision of educational programmes to be supported by mass media, devise mechanisms to extend distance and continuing education programs and supervise the implementation thereof;
6. cause to accord affirmative measures as regards to educational services given for women, children, adults and for persons with special needs;
7. train or cause to train teachers and other educational personnels in accordance with the national standards of training and give institutional as well technical support for Sub-City Education Offices and other bodies engaged in the sector;

፰ የአስተዳደሩ የትምህርት ተቋሞች ደረጃቸውን ያሚሉ መሆናቸውን ይቆጣጠራል፣ የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፣ ትምህርት ቤቶችን ማቋቋም ለሚፈልጉ ባለሀብቶች የመረጃ አገልግሎትና ድጋፍ ይሰጣል፣ በሀገር ውስጥም ሆነ በዉጭ ባለሀብቶች የሚቋቋሙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የብቃት ደረጃ መሚላ ቸውን ያረጋግጣል፤

፱ በከተማው ውስጥ የሚገኙ የግል ና ሌሎች መንግስ ዊ ባልሆኑ ተቋማት የሚተዳደሩ ትምህርት ቤቶችን በበላይነት ይመራል::

**፳. የኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ**

የኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ተጠሪነቱ ለትምህርት ቢሮ ሆኖ፣ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፲፪/፲፱፻፺፩ የተመለከተው ሥልጣንና ተግባር ንዲሁም አደረጃጀትና አሠራር ይኖረዋል::

**ዘርፍ ዘጠኝ**

**የንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮና በሥሩ ያሉ አስፈጻሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር**

**፳፩. የንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ**

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩ ል:-

፩ የኢንቨስትመንት ኤጀንሲንና የኤግዝብሽን ማዕከልን በበላይነት ያስተባብራል፣ ይመራል፤

፪.አጠቃላይ ንግድና ኢንዱስትሪ ልማትን በተመለከተ:-

ሀ. በኢንቨስትመንት ፖሊሲና ሕግ መሠረት ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ የኢንዱስትሪ ኘሮጀክቶችን ያመነጫል፤ ንዲጠኑና ሥራ ላይ ንዲውሉ ያደርጋል፤ንግድ፣ ኢንዱስትሪና ዕደ ጥበብ በከተማው ውስጥ ንዲስፋፋ ያደርጋል፣ ሕገወጥ ንግድን ከሚመለከተዉ አካል ጋር በመተባበር ይቆጣጠራል፣

ለ. የከተማው የምርት ውጤቶች በከተማው ውስጥና ውጭ ንዲ ወቁ ያደርጋል፤ በከተማው ውስጥና ውጭ አውደርዕይ ንዲዘጋጅ ያደርጋል፤ በክልሎች በሚዘጋጁ አውደ ርዕዮች ላይ ይሳተፋል፤

8. supervise educational institutions run by the Government with a view to ensure their compliance with the prescribed standard and accredit same; provide information service and other supports for investors who want to engage in the sector; ensure that high schools established by local as well as foreign investors are in compliance with the standards set forth;

9. direct schools administered by private and other non-governmental institutions in the City.

**20. Kotobe College of Teachers Education**

The College shall have the powers and duties as well as organizational structure and functions given to the Kotobe Teachers Education College of the Addis Ababa by Regulations No.12/1998 and shall be accountable to the Education Bureau.

***Section Nine***

***Powers and Functions of Bureau of Trade and Industry Development and the Executive Organs accountable to it***

**21. Bureau of Trade and Industry Development**

The Bureau shall have the following powers and functions to:

1. coordinate and direct the Investment Agency and Exhibitiokn Centre;
2. with respect to the overall development of trade and industry the Bureau shall:

a) initiate applicable industrial projects that are in accordance with the investment policy and law; cause them to be studied and implement same; initiate the expansion of trade, industry and handicrafts in the City; control illegal trade activity in cooperation with the concerned body;

b) publicize the City products inside and outside the City; initiate organization of exhibitions in and outside the City; participate in exhibitions organized by the Regional Governments;

ሐ. የአገር ውስጥ ባለሀብቶች በከተማው ውስጥ በንግድና ኢንዱስትሪ ሥራ ላይ በሰፊው ንዲሰማሩ ያበረ ል፤ የቴክኒክና የምክር አገልግሎቶችን ይሰጣል፤ በንግድ ሥራ ለሚሰማሩና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎችን ለሚያቋቁሙ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፤ በከተማው ውስጥ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ንዲቋቋም ያበረ ል፣ ድጋፍ ይሰጣል፣

መ. የከተማውን የንግድ መዝገብ ያቋቁማል፣ ያስተዳድራል፣ የንግድ ማሕበራትን በሕግ መሠረት በመመዝገብ ፈቃድ ይሰጣል፤ ያድሳል፣ ያግዳል፣ ይሰርዛል፣ የዋስትና መያዣ በሕግ መሠረት በንግድ መዝገብ ይመዘግባል፣ ይሰርዛል ለሃራጅ ሽያጭ አፈጻጸም የሚረዱ ስራዎችን በሕግ መሠረት ያከናውናል፤

ሠ. የገበያ ማዕከላትን ደረጃ ያወጣል፤ ደረጃቸውን የጠበቁ የገበያ ማዕከላት መገንባ ቸውን ይቆጣጠራል፣ የሚስፋፉበትንና የሚያድጉበትን ሥልት ይቀይሳል፤

ረ. በከተማው ውስጥ የመሠረ ዊ ንግድ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ሥርጭት የገበያ ሕግን ሥርዓትን መከተሉን፣ የፍጆ ምርቶች የአገልግሎት ዘመንና የተዘጋጁባቸው ንጥረ ነገሮች ይዘት ሽማቹ ማወቅ በሚችልበት ሁኔ መሆኑን፤ የአቅርቦት ሥርዓት መኖሩን በመከ ተል ገበያ በሚረጋጋበት ሁኔ መከናወኑን ያረጋግጣል፤ ለነጻ ገበያ ውድድር ንቅፋት የሆኑ ድርጊቶችና ተገቢ ያልሆኑ የንግድ ስራዎች ንዳይፈጸሙ በመከላከልና በማስወገድ የከተማውን ነዋሪዎች ጥቅም ያስጠብቃል፤ የገበያ ዋጋ መረጃ በመሰብሰብ፣ በመተንተን፣ በማቀነባበር ጥናቶችን ያደርጋል፣ ለፖሊሲ አውጪው አመላካች ሃሳብ ያቀርባል፤

c) encourage wider participation of local investors in trade and industrial activities; render technical and counseling services; issue license and supervise local investors engaged in trade and that established medium size industries in the City; encourage and support establishment of chambers of industry and commerce in the City;

d) Organize and administer the commercial registry of the City; in accordance with the law, issue, renew, suspend, cancel license for business organizations; register and revoke mortgages;facilitate auction sales in accordance with the law;

e) issue standard for market centers; supervise the construction of market centers in accordance with the standard; design strategies for expansion and development of same;

f) ensure undertaking of market stabilization activities by following up that distribution of basic commodities and services are in accordance with the law of market system, consumer goods are clearly marked with their expiry time and composition, the supply system is in place; protect the interest of the City residents by avoiding unfair business practices and removing obstacles to free market operation; conduct studies by collecting, compiling, and analyzing market information and submit proposal to policy makers.

ሰ. ለገበያ የሚቀርቡ ምርቶችና አገልግሎቶች ጥራትና ደረጃቸው የተጠበቀ መሆኑን፣ የልኬት መሣሪያዎችና መስፈሪያዎችን ትክለኛነት ያረጋግጣል፣ ይቆጣጠራል፣ ጥራትና ደረጃቸው ያልተጠበቀ ወይም ጊዜ ያለፈባቸው ምርቶች ና ትክክለኛ ሆነው ያልተገኙ የልኬት መሣሪያዎችንና መስፈሪያዎችን ያሰወግዳል፣

ሸ. በከተማው አስተዳደር ለገበያ አገልግሎት ንዲውሉ የተዘጋጁ ቦ ዎችን፣ ተለጣፊ ሱቆችን በለስላሣ መጠጥ ፋብሪካዎች የተገነቡ መደብሮችን ይቆጣጠራል፤ ያስተዳድራል፣ የአገልግሎት አሰጣጡን በተመለከተ መመሪያ ያወጣል፣

፫. የከተማ ግብርና ልማትን በተመለከተ፡-

ሀ. በከተማው ውስጥ የግብርና ምርት በጥራት የሚመረትበትንና ለገበያ የሚቀርብበትን ንዲሁም የግብርና ልማት የሚጎለብትበትን፣ የኢንቨስትመንት ሥራ የሚስፋፋበትን ስልት ይቀይሳል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ መሆኑን ያረጋግጣል፤

ለ. ለከተማ ግብርና ዘርፍ ድገት ድጋፍ የሚገኝበትን ዘዴ አጥንቶና ፕሮጀክት ቀርጾ ያቀርባል፣ ድጋፍ ሲገኝም ተግባራዊ ንዲሆን ያደርጋል፣ በግብርናው ዘርፍ መረጃዎችን በማሰባሰብ፣ በማጠናቀርና በመተንተን ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል፣

ሐ. የ ንስሳት በሽ ዎችን ሥርጭት ያጠናል፣ በበሽ ስርጭት የተነሳ መወሰድ ያለባቸውን ርምጃዎች ለመንግስትና ለአርቢዎች ያሳውቃል፤ ለ ንስሳት አርቢዎች፣ የ ንስሳት ህክምናና ክትባት አገልግሎት ይሰጣል፣ ንዲሰጥ ያደርጋል፣ ንዲሁም የ ብድ ዉሻ በሽ የመከላከያ ክትባት ይሰጣል፣ ባለቤት የሌላቸውን ውሾች ያስወግዳል፣

መ. ለ ንስሳት አርቢዎች የማዳቀል አገልግሎት ይሰጣል፣ የተሻሻሉ የግብርና ቴክኖሎጂ ውጤቶች፣ ምርጥ ዘርና ማዳበሪያ ለገበሬዎች ንዲዳረስ ሁኔ ዎችን ያመቻቻል፣ ወጤ ቸውንም ይከ ተላል፣ ለገበሬዎች ትምህርትና ሥልጠና ንዲሁም የሙያ ድጋፍ ይሰጣል፤

g) ensure and control that products and services supplied to the market are up to the standard, the instruments of measurement are correct; dispose products below standard or expired and the instruments of measurement;

h) control and administer places designated for market service, small shops; issue directive regarding the service delivery;

3. With respect to Urban Agriculture, the Bureau shall:

a) design strategies for the production and supply of quality agricultural products and for the expansion of investment that enhances agricultural development in the City and implement same upon approval;

b) study and submit strategies and projects for soliciting support for development of urban agriculture sector; collect, compile and analyze information in the agricultural sector and dessiminate to users;

c) study distribution of animal diseases; notify measures to be taken to Government and animal breeders'; provide or cause the provision of animal vaccination and treatment services to breeders; and also give vaccination against rabis and avoid domestic dogs that have no owners.

d) give cross-breeding services to animal breeders; facilitate the condition for the supply of improved agricultural technology, selected seed and fertilizer to farmers and follow-up their activities; give education and training and also technical support to farmers.

ሠ. የአስተዳደሩን የ ንስሳት ማራቢያና ማባዣ ማዕከላትን ያቋቁማል፣ ያስፋፋል፣ ያስተዳድራል፣ የአስተዳደሩን የብዝሀ-ሕይወት ቤተ ሙከራዎችን ያስተዳድራል፣ የምርምር ወጤቶችን ገበሬዎች ንዲጠቀሙባቸው ያደርጋል፤

ረ. የ ንስሳት ቆዳና ሌጦ ሀገር አቀፍ ደረጃን መሠረት በማድረግ በጥራት መመረ ቸውን ያረጋግጣል፤ ተገቢዉን ድጋፍ ይሰጣል፤

ሰ. የ ንስሳትና የ ጽዋት የኳራንቲን አገልግሎት ይሰጣል፣ በከተማው ውስጥ አገልግሎት ላይ ሊወሉ የሚችሉ

ረ. የ ንስሳት መድሃኒቶች የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁና የአገልግሎት ዘመናቸው ያላለቀ መሆኑን ያረጋግጣል፤ የአገልግሎት ዘመናቸዉ ያለቀ መድሀኒቶችን በኮሚቴ አማካይነት ያስወግዳል፤

ሸ. ለ ንስሳት ለሰብል፣ ለአትክልትና ፍራፍሬ ገበያዎችና ንዲሁም በከተማው ውስጥ በማስተር ፕላኑ ለከተማ ግብርና የተከለሉ ቦ ዎችንና ለቄራ የሚሆኑ ቦ ዎችን ከሚመለከተው የአስተዳደሩ አካል ጋር በመመካከር ንዲዘጋጁና በዘመናዊ መንገድ ንዲሰሩ ያደርጋል፣

ቀ. በግል የሚቋቋሙትን የ ንሰሳት ጤና ክሊኒኮች፣ ላብራቶሪዎች፣ የቆዳና ሌጦ መጋዘኖች፣ ጸረ-ተባይ ማከማቻ መጋዘኖችና መሸጫ መደብሮች ደረጃና ጥራት ጠብቀው በሕግ መሠረት መስራ ቸውን ይከ ተላል፣ ይቆጣጠራል፤

በ. በህግ በሌላ ሁኔ የተደነገገው ንደተጠበቀ ሆኖ በመንግስት፣ በማህበራት ና በግል ቄራ ድርጅቶች የሥጋ ምርመራ አገልግሎት ይሰጣል፣ ጤናማ ሥጋ ለተጠቃሚዎች መቅረቡን ያረጋግጣል፣ ንዲሁም ሕገወጥ የ ንስሳት ርድና በሕገወጥ መንገድ የ ረደ ስጋ ዝውውርን ይቆጣጠራል፣ በሥጋ ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች የምርት ጥራትና የሐይጅን ቁጥጥር ያካሂዳል::

e. organize, expand and administer animal breeding and multiplication centers in the City; administer the bio-diversity laboratory of the Government; cause farmers to use research findings;

f. ensure that animal skin and hides are produced according to the national quality standard; provide the necessary support;

g. give quarantine control services on animals and plants; ensure that the veterinary drugs in the market are in accordance with the standard and the date for the use of such drug is not expired; discharge expired drugs through committee;

h. in collaboration with the concerned Government organ, cause the arrangement and modern management of market centers for animals, crops and horticultures and designation of places for urban agriculture and abbiators in accordance with the master plan;

i. follow- up and supervise private veterinary clinics, laboratories, hides and skin stores, pesticides storage and sales shops to ensure their compliance to the required quality and standard in accordance with the law ;

j without prejudice to provisions stated in other laws, give meat inspection services to governmental, associations and private abbiators ; ensure the supply of healthy meat to consumers ; control illegal slaughters and movement of illegally slaughtered meat ; undertake supervision of product quality and hygiene of meat processing factories ;

፬. የሕብረት ሥራ ማህበራት ልማትን በተመለከተ:-

ሀ. የህብረት ሥራ ማህበራትን በፌዴራል የሕብረት ስራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር ፻፵፯/፲፱፻፺፩ ( ንደተሻሻለ) ንዲሁም የጋራ ህንፃ ባለቤቶች ማህበራትን በጋራ ሕንፃ ህግ በተደነገገው መሠረት ያደራጃል፣ ይመዘግባል፣ ያስፋፋል፣ የሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ ማህበሩ ሲፈርስ ከመዝገብ ይሰርዛል፤

ለ. የሕብረት ሥራ ማህበራት ባንኮች የሚያቋቁሙበትን መንገድ ያጠና ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

ሐ. የህብረት ስራ ማህበራት ጽንሰ ሃሳብን ለማስፋፋትና ለማዳበር የሚያስችሉ ተከ ይ የትምህርትና የስልጠና ፕሮግራም ያዘጋጃል፣ ይሰጣል፣ ከሚመለከ ቸው አካላት ጋር በመተባበርም የአገር ውስጥና የውጭ አገር ስልጠናና የትምህርት ድሎች የሚገኝበትን ስልት ይቀይሳል፤

መ. የህብረት ሥራ ማህበራት ስራ አመራር የሂሳብ አያያዝ ዘመናዊ አሰራርን ንዲከተል አስፈላጊውን የትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራም ያዘጋጃል፣ ይሰጣል፤

ሠ. የሕብረት ስራ ማህበራትን ለማስፋፋትና ለማጠናከር የሚረዳ የገበያ ጥናት በማድረግ አስፈላጊ መረጃዎችን ያሰራጫል፣ ስ ትስቲካዊ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያቀናብራል፣ ለሚመለከተው አካል ያስተላልፋል፣ ንዲሁም በፌዴራል የሕብረት ስራ ማህበራት አዋጅ የተደነገገው ንደተጠበቀ ሆኖ፣ ለህብረት ሥራ ማህበራት የሚሰጡ ማበረ ቻዎችን ያጠናል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ መሆኑን ያረጋግጣል፤

ረ. የህብረት ስራ ማህበራት ሞዴል መተዳደርያ ደንቦችን አዘጋጅቶ በስራ ላይ ያውላል፤

ሰ. አግባብ ካላቸው መንግስ ዊና መንግስ ዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር የቅርብ ግንኙነት በመፍጠር የህብረት ሥራ ማህበራት ተገቢ ድጋፍና ገዛ ንዲያገኙ ጥረት ያደርጋል::

4. With Respect to Cooperatives Development, the Bureau shall :

a) organize, register, promote, give certificate of legal personality to cooperatives in accordance with the Federal Government Revised Proclamation No. 147 of 1998 and to associations of owners of condominiums and revoke same upon their dissolution ;

b) study and sumbmit ways for the establishment of cooperative banks and implement same upon approval ;

c) prepare and provide successive educational and training programmes that enable to promote and develop the concept of co-operative; it shall in collaboration with concerned organs, devise means by which domestic as well as external training and educational opportunities are obtained;

d) Prepare and offer the necessary education and training program with the view to modernize the management and accounting system of cooperatives;

e) upon conducting market study, dessiminate information required for promoting and strengthening cooperatives; collect, compile statistical data and submit to the appropriate organ; without prejudice to the provisions stated in the federal cooperative proclamation, conduct study on incentives for cooperatives, and ensure implementation of same upon approval;

f) prepare and implement model by-laws of cooperatives;

g) make effort to solicite support and assistance for cooperatives by creating close relationship with appropriate Governmental and Non-Governmental organizations.

www.chilot.me

**፳፪. የኢንቨስትመንት ኤጀንሲ**

ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩ ል:-

፩ የከተማውን የኢንቨስትመንት ንቅስቃሴዎች ያስተባብራል፣ ያስፋፋል፣ ያበረ ል፣ ምክርና የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፣

፪ የከተማውን የኢንቨስትመንት አመቺነት በዝርዝር በማጥናት በልዩ ልዩ መንገዶች ለኢንቨስተሮች ያስተዋውቃል፤

፫ በሥልጣኑ ክልል ሥር የሚወድቁ የኢንቨስትመንት ጥያቄዎች ሲቀርቡለት በሕግ መሠረት መርምሮ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ማግኘት የሚያስችሉ መረጃዎች መሟላ ቸውን በማረጋገጥ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ይሰጣል፣ የንግድና ኢንዱስትሪ ፈቃድ ማግኘት ንዲችልም አግባብ ወዳለው አካል ያስተላልፋል፤

፬ ለኢንቨስትመንት ተቋማት የማምረቻና የመሸጫ ቦ ዎች፣ የፋይናንስና የብድር አገልግሎቶች፣ የጥሬ ዕቃና የማምረቻ መሳሪያዎች በዝቅተኛ ዋጋ የማግኘት ዕድልና የተለያዩ የመሠረተ ልማት አው ሮች የሚሟሉበትን ሁኔ ያመቻቻል::

***ዘርፍ አሥር***

***የኮንስትራክሽንና ቤቶች ልማት ቢሮ እና የሚያስተባብራቸው አስፈፃሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር***

**፳፫. የኮንስትራክሽንና ቤቶች ልማት ቢሮ ፡-**

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤-

፩ የቤቶች ግንባታ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤትን፣ የቤቶች ልማት አስተዳደር ኤጀንሲን፣ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማትና ቁጥጥር ባለሥልጣንን፣ የመንግስት ኮንስትራክሽን ኤጀንሲን እና የህብረተሰብ ተሣትፎ ልማት ኤጀንሲን በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፤

**22. Investment Agency**

The Agency shall have the following powers and functions :

1. coordinate, promote and encourage the investment activities of the City; render the necessary advice and technical support;
2. conducting detail studies, and publicize the favourable investment opportunities of the City to investors;
3. issue investment license upon requests for investment permits that fall under its jurisdiction verify that the required documents are produced in accordance with the law, transfer the matter to the appropriate organ for the issuance of trade and industrial license;
4. facilitate ways for the provision of production and sales centers, financial and loan services, the opportunity to get raw materials and machinery with low prices and the fulfillment of various infrastructures for investment enterprises.

***Section ten***

***Power and Function of Construction and Housing Development Bureau and Executive Organs it Coordinates***

**23. Construction and Housing Development Bureau**

The Bureau shall have the following powers and functions:-

1.superiorly direct and coordinate the Housing Construction Project Office, Housing Development and Management Agency, Construction Industry Development and Regulatory Authority, Government Construction Agency, and Public Participation and Development Agency;

፪ በአስተዳደሩ በጀት ለሚሰሩ የኮንስትራክሽን ሥራዎች ዲዛይኖች እንዲሁም የቤቶች ግንባታ እና ሌሎች ቢሮዉ የሚመራቸዉ ግንባታዎች የሚመለከቱ ውሎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤

፫ በሚመለከተው የፌደራል መንግሥስት አካል የሚፈፀመው እንደተጠበቀ ሆኖ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን የአቅም ክፍተት በጥናት ላይ ተመስርቶ እንዲሞላ ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፣ አፈፃጸሙን ይከታተላል፤ አቅም ለመገንባት የሚጠቅሙ አዳዲስ አማራጭ ቴክኖሎጂዎችን የማፈላለግና የማሻሻል ሥራዎች እንዲከናወኑ ይደግፋል፤ ያስተባብራል የተገኙትም ሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

፬ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን ዕድገት ከግብዓት አቅርቦት ጋር መጣጣም እንዲችል የግንባታ ግብዓት አምራቾችና አከፋፋዮች በጥራትና በብዛት እንዲያቀርቡ ስትራቴጂዎችን ይነድፋል፣ ይደግፋል፣ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤

፭ የኮንስትራክሽን ዘርፍ የመረጃ መረብና ማዕከል እንዲኖር በማድረግ ወቅታዊ የዘርፉ መረጃዎች ተሰብስበው፣ ተመዝግበውና ተተንትነው የልማት አቅጣጫዎችን መጠቆም በሚችሉበት አግባብ መደራጀታቸውን ያረጋግጣል፤

፮ የከተማው የቤት ልማት ሥራ ከሥራ ፈጠራና ከዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ጋር የተቀናጀ እንዲሆን ጥናቶችን ያካሂዳል ለተግባራዊነታቸውም ድጋፍ ይሰጣል፣

2. cause the preparation, in cooperation with the concerned bodies, contracts regarding construction works undertaken by budget of the City Government as well as housing construction and other constructions the Bureau directs; follow up implementation of same;
3. notwithstanding implementation by the concerned body of the Federal Government, provide appropriate support towards fulfilling the capacity gap of the construction industry based on research; cause the performance of searching and improving new alternative technologies that help to build capacity; coordinate same and ensure that such technologies are utilized;
4. design strategies whereby producers and retailers of construction inputs supply in large quantity and better quality with the view to harmonize supply of the input with development of the construction industry; support and follow up implementation of same;
5. ensure that, causing existence of data network and center, current data of the construction section is collected, recorded, analysed and organized in a manner that it can indicate development directions;
6. conduct researches with the view to coordinate the housing development works of the City with job creation and the Growth and Transformation Plan; provide support to the implementation of same;

፯ በአስተዳደሩ የሚገነቡትን የመኖርያ ቤትና ሌሎች የአስተዳደሩ ግንባታዎችን ይከታተላል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ለተነሺዎች መጠለያ መቅረቡን ያረጋግጣል፤ እንዲሁም በመንግስትና በሌሎች አካላት ለሚገነቡ የጋራ መኖርያ ቤቶች የመሠረተ ልማት አቅርቦት እንዲሟላ የሚመለከታቸውን አካላት ያስተባብራል፣

፰ በአስተዳደሩ ስር የሚተዳደሩ ቤቶች በሕግ አግባብ ለተጠቃሚው አገልግሎት መዋላቸውንና አዲስ የሚገነቡ ቤቶችም በህግ አግባብ ለተጠቃሚዎች መተላለፋቸውን ያረጋግጣል፤

፱. በከተማ አስተዳደሩ ባለቤትነት ሥር ያሉ የመኖሪያና የንግድ ቤቶች በሽያጭ ወደግል ባለቤትነት የሚዛወሩበትን ሁኔታ ተጠንቶ ሲቀርብለት በካቢኔ በሚቀመጥ አቅጣጫ መሠረት ጥናቱን መርምሮ ያፀድቃል፣ ተግባራዊነቱን በበላይነት ይከታተላል፣

፲. ከከተማዉ አስተዳደር ዉጪ በበጎ አድራጊ ወይም በሌላ የከተማዉን ኅብረተሰብ የቤት ወይም ሌላ ማህበራዊ ችግር ለመቅረፍ የሚሰሩ ግንባታዎች ወይም ለግንባታ የሚሰጥ ገንዘብ በአግባቡ ለታሰበዉ ዓላማ መዋሉን ይቆጣጠራል፣ አግባብነት ባለዉ ህግ መሠረት ያስዳድራል፤

፲፩. በአስተዳደሩ በጀት እና በሕብረተሰብ ተሳትፎ የሚሰሩ የግንባታ ሥራዎችን ያስተባብራል፤ ይመራል፣

፲፪. በአስተዳደሩ የሚከናወኑ ማናቸውም የቤት ግንባታ ሥራ በተገባለት ውል መሰረት የጥራት ደረጃቸውን፣ የጊዜና የዋጋ ገደቡ ተጠብቆ መሰራቱን ለማረጋገጥ የሚያስችል የቁጥጥር ሥርዓት እንዲኖር ያደርጋል፤ በበላይነትም ይቆጣጠራል፤

7. follow up the construction of residential houses and others carried out by the City Government; ensure that shelter is provided to persons displaced in coordination with the concerned bodies; as well coordinate the concerned bodies towards fulfillment of infrastructure for condominiums built by government and other bodies;

8. ensure that the houses administered by the City Government are meant for the service of beneficiaries and also newly built houses are properly transferred to the beneficiaries in accordance with law;

9. approve, based on direction set by the Cabinet, upon investigating the research submitted regarding conditions by which residential and commercial houses belonging to the City Government are to be transferred to private ownership and superiorly follow up implementation of same;

10. administer and supervise the construction or finance, other than that of the City Government, given with the objective of alleviating the housing or other social problem of residents of the City by donors or others is used for the objective sought;

11. direct and coordinate construction works undertaken by budget of the City Government and public participation ;

12. cause the establishment of control system that enables to ensure any housing construction work undertaken by the City Government is carried out in accordance with the quality, time and cost specified in the contract; superiorly direct same;

፲፫.ለጎርፍ የተጋለጡ የከተማዋን ክፍሎች በተመለከተ የመከላከል ሥራው ያለበትን ደረጃ ይገመግማል፣ ድጋፍ ያደርጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

፲፬ የከተማውን የቤት ችግር ከመቅረፍ አንፃር በቤቶች ግንባታ ዘርፍ አስፈላጊ ሲሆን ከቤቶች ግንባታ ፕሮጀክቱ ውጪ ያሉ አካላት እንዲሳተፉ ያደርጋል፣

## ፳፬. የቤቶች ግንባታ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት

፩. ፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ በቦርድ የሚመራ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤-

ሀ. የቤቶች ልማትና አስተዳደር ኤጀንሲ በሚያቀርበው የቤት ፍላጎት መነሻነት ለከተማዋ ነዋሪዎች ግልጋሎት የሚውል ምቹና ተደራሽ መኖሪያ ቤቶች ይገነባል፣ እንዲገነቡ ያደርጋል፣

ለ. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ለሚሰራቸው ወይም ለሚያሰራቸው መኖርያ ቤቶች የተሳለጠ የመሬትና የመሰረተ ልማት አቅርቦት መኖሩን ያረጋግጣል፣

ሐ. ወጭ ቆጣቢ የሆኑ አዳዲስ አማራጭ የቤቶች ግንባታ ግብአት ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀምና በማስፋፋት የግንባታ ኢንዱስትሪውን ያጠናክራል፣

መ. የቤቶች ልማት ፕሮግራም የተሳካ እንዲሆን የአግሮስቶን እና ተጓዳኝ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት በከተማዉ አስተዳደር እንዲቋቋሙ ያደርጋል፣ ከፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ ፍላጎት በላይ የሆኑ ምርቶችን ለሽያጭ ያቀርባል፣ የሚያመርታቸውን ምርቶች ሥራ ላይ ከማዋልና ከመጠቀም ጋር የተያያዙ ሥልጠናዎችን እና ሌሎች አገልግሎቶችን ይሰጣል፤

ሠ. ለቤቶች ልማት ፕሮግራም አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶችና የግንባታ ዕቃዎችን ከአገር ውስጥ ይገዛል፤ ዕቃዎቹ ከውጪ መገዛት ያለባቸው መሆኑ ታምኖበት በሚመለከተው አካል ሲወሰን የመንግስትን የግዥ ሕግን ተከትሎ ዕቃዎቹን ከውጭ አገር ይገዛል፣ ወይም እንዲገዛ ያደርጋል፤

13. cause organs other than the housing construction project to participate in the housing construction sector, where necessary, with the view to solve the housing problem of the City;

14. evaluate, provide support and follow up implementation as regards level of the prevention work in parts of the City exposed to flood.

## 24. Housing Construction Project Office

1. The project office, being directed by board, shall have the following powers and functions:-

a. construct or cause the construction of convenient and accessible residential houses that serve the residents of the City based on the demand identified by the Housing Development and Management Agency;

b. in coordination with the concerned bodies, ensure the availability of land and infrastructure for the houses it constructs or causes to be constructed;

c. strengthen the construction industry by applying and disseminating cost minimizing and new alternative house construction input technologies;

d. cause establishment of agrostone and related service institutions by the City Government for success of the housing development programme; supply for sale products which are beyond the needs of the project office; provide training and other services related to the use and application of such products;

e. purchase or cause the purchase of goods and construction materials necessary for the housing development programe; where it is believed and decided by the concerned body that such should be bought from abroad it shall effect or cause same in accordance with procurement laws of the government;

www.chilot.me

ረ. ከዲዛይን እስከ ኮንስትራክሽን ያሉት የስራ ሂደቶች ደረጃቸውን እንዲጠብቁ በማድረግ የቤት ልማት ፕሮግራሙ በቅልጥፍና እንዲከናወን ያደርጋል፣

ሰ. ለቤቶች ግንባታ የሚያስፈልገውን ዝርዝር የአካባቢ ልማት ፕላንና ዲዛይን ከከተማ ፕላን ጋር በሚስማማና ወጪ በሚቀንስ ሁኔታ በከተማ ፕላን ኢንስቲትዩት እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣

ሸ. ግንባታቸው ፹% በላይ የደረሱ ቤቶችን ብዛት በቤቶቹ አይነት ለይቶ በሰነድ ደረጃ እና እነዚሁ ቤቶች ግንባታቸዉ ተጠናቆ ፻% ሲደርስ የግንባታ ወጪውን ጭምር አንድ ላይ በማድረግ ቤቶቹን ለቤቶች ልማትና አስተዳደር ኤጀንሲ ያስተላልፋል፣

ቀ. እንደ አስፈላጊነቱ በአስተዳደሩ ወይም በቦርዱ ሲታዘዝ ዓላማውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ሌሎች ተዛማኝ ተግባራትንና ግንባታዎችን ያከናውናል።

፪ ስለ ቦርድ አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባራት ዝርዝሩ በከተማዉ አስተዳደር ካቢኔ በሚወጣ ደንብ ይወሰናል።

## ፳፭. የቤቶች ልማትና አስተዳደር ኤጀንሲ

ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤-

፩ በከተማው አስተዳደር የቤቶች ግንባታ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት የተገነቡና የተጠናቀቁ ቤቶችን አግባብነት ካላቸው ሠነዶች ጋር ይረከባል፤ በየቤቶቹ አይነትና አገልግሎት መረጃዎችን ይመዘግባል ያደራጃል፤ ለተጠቃሚው በህግ መሠረት ያስተላልፋል፣

፪ ኤጀንሲው በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሰው ቢኖርም ለዕጣ ማውጣት ሂደቱ አመቺ እንዲሆን የግንባታ ሂደታቸው ፹% በላይ የደረሱ ግንባታዎችን በየቤቶቹ አይነት ለይቶ በሰነድ ደረጃ ከፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ በመረከብ ዕጣ ያወጣል፣

f. cause the speedy performance of the housing development programme by making the work process from design up to construction maintain the standards;

g. cause the preparation of the detailed local development plan and design necessary for the housing construction in a manner compatible with urban plan and cost minimizing condition by the Urban Plan Institute;

h. transfer to the Housing Development and Management Agency document of houses the construction of which is accomplished more than 80% by identifying them in type and those the construction of which is accomplished 100% along with their cost of construction;

i. perform as may be necessary such other related functions and constructions designated by the City Government or Board which help in achieving its objectives.

2. Details about the organizational structure, powers and functions of the board shall be determined by regulation issued by Cabinet of the City Government.

## 25. Housing Development and Management Agency

The Agency shall have the following powers and functions:-

1. receive houses constructed by the Housing Construction Project Office of the City Government which are accomplished, along with the appropriate documents; record and organize data according to the type and service of the houses; transfer to beneficiaries according to law;
2. notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, the Agency shall draw lot up on receiving from the Housing Construction Project Office houses, the construction of which is more than 80% accomplished, by categorizing into type of houses with the view to facilitate the drawing of lot;

፫ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሰረት የተረከባቸውን ቤቶች ከማስተላለፉ በፊት በጋራ ህንፃ ህግ መሰረት በተደራጁ የባለቤቶች ማህበር እንዲተዳደር አስፈላጊውን አሟልቶ በሚመለከተዉ አካል በኩል እንዲመዘገብ ያደርጋል፣

፬ በተለያዩ ደረጃዎች የሚገኙ ቤት ፈላጊዎችን ብዛትና ቁጥር ለማወቅ የሚያስችል ምዝገባ ያካሂዳል፤ መረጃውን ያደራጃል ወይም በየክፍለ ከተማው እንዲደራጁ ያደርጋል፣

፭ አማራጭ የፋይናንስ ምንጮችን በማጥናት ህብረተሰቡ የቤት ባለቤት ሊሆን የሚችልበትን ጥናት በከተማዉ አስተዳደር ካቢኔ ሲጸድቅ በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

፮ የከተማዉ አስተዳደር ለቤቶች ግንባታ የተበደረዉ ገንዘብ በወቅቱ እንዲመለስ ቤት ከተረከቡ ግለሰቦች ገንዘብ ባግባቡ መሰብሰቡን ይከታተላል፤

፯ በከተማ አስተዳደሩ ባለቤትነት ሥር ያሉ የመኖሪያና የንግድ ቤቶችን አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ሙሉ መረጃ በመያዝ ይመዘግባል፤ ያከራያል፤ ያስተዳድራል፤ በሽያጭ ወደግል ባለቤትነት የሚዛወሩበትን ሁኔታ አጥንቶ ለቢሮው ያቀርባል፣ በቢሮው ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፣

፰ በከተማው አስተዳደር ባለቤትነት ሥር ያሉትን ህንጻዎች ይመዘግባል፣ ቤቶቹ የሚሻሻሉበትን ሁኔታ አጥንቶ በቢሮዉ በኩል ለከተማ አስተዳደሩ እንዲቀርብ ያደርጋል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፡

፱ እንዳስፈላጊነቱ በከተማ አስተዳደሩ ወይም በቢሮዉ ሲታዘዝ ዓላማውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ሌሎች ሥራዎችን ያከናውናል፡፡

3. cause the houses it received in accordance with sub-article (1) of this Article to be registered through the concerned body, before it transfers, upon fulfillment of the necessary requirements to be administered by association of owners organized in accordance with condominium law,
4. carry out registration that enables identify quantity and number of house seekers at different levels; organize the data or cause it to be organized at each Sub-city;
5. conduct study on alternative finance sources whereby residents of the City become owner of house; cause same implemented upon approval by Cabinet of the City Government;
6. follow up proper collection of the cost of houses from the beneficiaries with the view to enable the City Government timely pay the loan it earned for the construction of houses;
7. register, with full information thereof, let and administer in accordance with appropriate law all residential and commercial houses belonging to the City Government, study conditions whereby such houses can be transfered to private owners on sale basis, implement same up on the approval by the Bureau;
8. register buildings belonging to the City Government, study conditions by which such buildings shall be improved and cause submission of same to the City Government through the Bureau, follow up the implementation upon approval;
9. perform, as may be necessary, such other activities designated by the City Government or Bureau that enable fulfillment of its objectives.

**፳፮. የመንግስት ግንባታዎች ኤጀንሲ**

ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩ በከተማ አስተዳደሩ የሚከናወኑ ከቤቶች፣ መንገዶችና ዉሀ ግንባታ ውጪ ያሉ የሌሎች የግንባታ ፍላጎቶችን በመቀበል ጥናት ያደርጋል፣ ዲዛይን ያዘጋጃል ከተቋሙ አቅም በላይ መሆኑ በቢሮዉ ሲረጋገጥ ዲዛይኑ በግል አማካሪ ድርጅት እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤

፪ የጨረታና የግንባታ ሂደቱን ከግንባታው ባለቤት ጋር በመሆን ያከናውናል፤ያስተባብራል፤ ይመራል፣ የግንባታ ውሎች የግንባታ ሕግን መሰረት በማድረግ እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

፫ ግንባታዎች በጸደቀው ዲዛይን እና ውል መሰረት መሰራታቸውን እና ጥራትና ደረጃቸውን የጠበቁ መሆኑን ባለሙያ በመመደብ ይቆጣጠራል፣ ከተቋሙ አቅም በላይ መሆኑ በቢሮዉ ሲረጋገጥ በግል አማካሪ ድርጅት አማካይነት ክትትል ያደርጋል፣

፬ የተለያዩ የግንባታ እና የዲዛይን አሰራር ማንዋሎችን እና ስታንዳርዶችን ያዘጋጃል፣ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤

፭ ለጎርፍ የተጋለጡ የከተማ ክፍሎችን በተመለከተ ጥናት ያደርጋል፣ እንዲጠና ያደርጋል፤ የመከላከያ ሥራ ለመሥራት ዲዛይን ያዘጋጃል፣ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ ለግንባታው ጨረታ ያወጣል፣ ግንባታውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡

**26. Government Construction Agency**

The Agency shall have the following powers and functions:-

1. undertake research on demands of construction undertaken by the City Government, with the exception of housing, roads and water construction; prepare design or cause the design to be prepared by private consultant where it is ascertained by the Bureau that the work is beyond capacity of the Agency;
2. perform, coordinate and direct the auction and progress of the construction together with the owner of the construction, cause construction contracts prepared in accordance with construction law; follow up and supervise the implementation of same;
3. supervise that constructions are carried out in accordance with the approved plan and contract by deploying experts; follow up through private consultant organization where it is ascertained by the Bureau that the work is beyond capacity of the Agency;
4. prepare or cause the preparation of different construction and design work manuals and standards;
5. undertake study or cause the undertaking of same on areas of the City endangered with flood; prepare or cause the preparation of design for carrying out protective work; give auction for the construction work; follow up and supervise the construction.

## ፳፯. የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማትና ቁጥጥር ባለሥልጣን

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩. በከተማው አስተዳደር ክልል ውስጥ የግንባታ ዘርፉና የመሠረተ ልማት አውታር የሚመራበትን የሕግ ማዕቀፎች ያዘጋጃል፤ ሲፀድቅም ተፈጻሚነታቸውን ይከታተላል፤

፪ አግባብነት ባለው የፌደራል መንግስት አካል የሚወሰነው እንደተጠበቀ ሆኖ በከተማው አስተዳደር ክልል ውስጥ የግንባታዉን ኢንዱስትሪ የአቅም ክፍተት በጥናት ላይ ተመስርቶ ይሞላል፤ አዳዲስ አማራጭ ቴክኖሎጂዎችን ለማሻሻል ጥናትና ምርምር ያካሂዳል፣ ያፈላልጋል፤ ልምድ ይቀስማል፤ ያላምዳል፤ ያሰርፃል፤

፫ በከተማዋ የሚንቀሳቀሱ የኮንስትራክሽን ሴክተር አካላት ባለሙያዎችን፤ አማካሪዎችን፤ የስራ ተቋራጮችን፤ የግንባታ መሳሪያ አቅራቢዎችን ይመዘግባል የሙያና የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይሰጣል፤ ፈቃድ ያድሳል፣ ይሰርዛል፤ ሕጋዊ ፈቃድ ይዘው መስራታቸውን ያረጋግጣል፤

፬ የግንባታ ግብአትና የጉልበት የገበያ ዋጋ ከፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ጋር በማጥናት የዋጋ ተመን ያወጣል፤ በካቢኔ ሲጸድቅ ለአስተዳደሩና ለዘርፍ ተጠቃሚ አካላት ያሰራጫል፤

፭ በግንባታዉ ዘርፍ ከዉል ጋር የሚከሰቱ አለመግባባቶችን በቅድሚያ በማየት ይፈታል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣

፮ የግንባታ ዘርፍ የመረጃ መረብና ማዕከል እንዲኖር ያደርጋል፤ መረጃዎችን ይመዘግባል፤ ወቅታዊ ያደርጋል፤ ይተነትናል፤ ውጤቱን ለህትመት ያበቃል፤ ያሰራጫል፣

## 27. Construction Industry Development and Regulatory Authority

The Authority shall have the following powers and functions:-

1. prepare legal framework governing the construction sector and infrastructure development works within boundary of the City; follow up implementation of same up on approval;
2. notwithstanding what is decided by the concerned organ of the Federal Government, fill the capacity gap of the construction industry in the City based on study; search for and conduct study on new alternative technologies; share experience; adopt and internalize same;
3. register and issue license of profession and competency to construction professionals, consultants, contractors and suppliers of construction materials in the City; renew, terminate the license; and ascertain that they are working with legal license;
4. issue price cost by undertaking research, in cooperation with the Finance and Economic Development Bureau, on construction input and labour market value; disseminate same to the beneficiaries of the sector as well as the City Government upon approval by the Cabinet;
5. resolve primarily disputes arising out of contracts of the construction sector; supervise the implementation thereof;
6. cause the existence of information network and center; register, update, analyze information thereof; publish the result and disseminate same;

፯. የግንባታ ግብአት ናሙናዎችን ከማምረቻ ቦታዎች በመውሰድ በላብራቶሪ ጥራታቸውን ያረጋግጣል፤ ችግር ባለባቸው ላይ አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፤ በተጠየቀ ጊዜ ለሌሎች ተቋማትና ግለሰቦች አስፈላጊውን ክፍያ በማስከፈል የግንባታ ግብአት የጥራት ምርመራ ያካሂዳል፣ ውጤቱንም ያሳውቃል፤

### ፳፰. የህብረተሰብ ተሳትፎ ልማት ኤጀንሲ

ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩ በከተማዋ ውስጥ በአካባቢ መሻሻል ለሚለሙ አካባቢዎች የልማት አፈፃፀም ስትራቴጂዎችን ነድፎ በቢሮው አማካይነት ለካቢኔ ያቀርባል፤ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፣

፪ ህብረተሰቡ የአካባቢውን ችግርና የልማት ፍላጎት እንዲለይ የልማቱ ቀጥተኛ ተሳታፊና የልማቱ አንቀሳቃሽ ኃይል እንዲሆን በየአካባቢው የልማት አደረጃጀቶች እንዲፈጠሩ ያደርጋል፣ ለአደረጃጀቶቹም የህግ ማዕቀፍ እንዲዘጋጅ በማድረግና በማስፀደቅ ሥራዎችን ይመራል ያስተባብራል፣

፫ አማራጭ የፋይናንስ ምንጮችን በመፈለግ ሲፈቀድ የአካባቢውን ህብረተሰብ የልማት ሥራ ያግዛል፤ ከህብረተሰቡ የሚሰበሰቡ የቁሳቁስ፤ የጉልበትና፤ የገንዘብ መዋጮዎች ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣

፬ በአካባቢው የተለዩ የህዝቡ ፍላጎቶች በሥራ ላይ የሚውሉበትን የግንባታ ፕላን እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ ለሚመለከተው አካል አቅርቦ ያስፀድቃል፤

7. confirm the quality of construction inputs through laboratory test by taking sample from production sites; take the necessary measure upon those with quality problem; undertake quality checking service to other institutions or individuals upon request by charging them the necessary fee.

### 28. Public Participation Development Agency

The Agency shall have the following powers and functions:-

1. design and submit development implementation strategies to the Cabinet through the Bureau, for areas within the City that are to be developed due to local upgrading; implement same up on approval;
2. cause the establishment of development structures in different parts of the City with the view to enable the society identify problems and development demands of the specific area, directly participate and become moving force of the development; coordinate and direct activities by causing preparation and approval of legal framework for such structures;
3. support developmental activities of a specific area by searching and upon approval of alternative financial sources; follow up the proper utilization of material, labour and monetary contributions of the society;
4. cause the preparation of construction plan that enables realization of demands of the society identified in the specific area; submit same to the concerned organ for approval;

፭ የህዝቡን ፍላጎት መሰረት አድርጎ የተሰራውን የግንባታ ፕላን ለመተግበር የሚያስችል የድርጊት መርሃ ግብር ያዘጋጃል፤ለተግባራዊነቱም ድጋፍ ያደርጋል፣

፮ በአካባቢ መሻሻል ልማት የሚለቀቅ ቦታ ካሳና ምትክ ቦታ የሚያስፈልገው ከሆነ ይህንኑ በመለየት ተገቢውን መስተንግዶ እንዲያገኙ ለሚመለከተው አካል ያሳውቃል፤ ክትትል ያደርጋል፤

፯ በአካባቢ መሻሻል ወቅት ለሚከናወን በኅብረተሰብ ተሳትፎ ለሚሠራ የግንባታ ስራ ዲዛይን ያዘጋጃል ወይም እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ የጨረታ እና የኮንትራት አስተዳደር ሥራዎችን ያከናውናል፤ የግንባታ ሂደቱን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

፰ የህብረተሰቡን ፍላጎት መሰረት ያደረጉ የአካባቢ ልማት ግንባታ ሥራዎች አጠናክሮ ነዋሪውን በማስተባበርና በማሳተፍ ማስቀጠል የሚያስችሉ ልዩ ልዩ የጥናት ሥራዎች በማከናወን ሲፀድቁ ሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤

፱ በህዝቡ የተከናወኑ የልማት ስራዎች በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ተገቢው ጥገናና ጥበቃ እንዲደረግላቸው ይከታተላል፣ ይደግፋል፤

፲ ምርጥ የህዝብ ተሣትፎ ተሞክሮዎችን ይለያል ፤ይቀምራል፤ ያስፋፋል፡፡

<u>ዘርፍ አሥራ አንድ</u>

**፳፱. የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ሥልጣንና ተግባር**

ቢሮው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩ ል:-

፩ የገቢዎች ባለሥልጣን ተጠሪነቱ ለከንቲባዉ መሆኑ ንደተጠበቀ ሆኖ ቢሮዉ ቴክኒካዊ በሆኑ ጉዳዮች ባለሥልጣኑን በበላይነት ይመራል፤ ያስተባብራል፤



5. prepare action plan enabling implementation of the construction plan prepared based on needs of the society; provide support for the implementation of same;
6. identify and inform to the concerned organ where a land to be cleared due to local upgrading deserves compensation and substitute plot of land for the purpose of appropriate service; follow up same;
7. prepare or cause the preparation of design for construction works done by public participation during local upgrading activities; undertake auction and contrat administering activities; follow up and control the construction process;
8. undertake different studies and cause the implementation thereof, up on approval, on how to scale-up local development construction activities done based on needs of the society by coordinating and participating the residents;
9. follow up and support the proper repair and conservation of developmental works carried out by the society with the view that they are properly utilized;
10. calper, compose and disseminate best practices of public participation.

<u>**Section seven**</u>

**29._Powers and Functions of Bureau of Finance and Economic Development**

The Bureau shall have the following powers and functions:

1. notwithstanding that the Revenue Authority is accountable to the Mayor, the Bureau shall coordinate and direct the activities of Authority as regards technical matters ;

፪ በከተማው አስተዳደር አካላት ተዘጋጅቶ የሚቀርብለትን የበጀት ጥያቄ ና የክፍለ ከተማዎችን የበጀት ድልድል መርምሮ የተጠቃለለ ዓመ ዊ በጀት ያቀርባል፤ ንደአስፈላጊነቱ ተጨማሪ በጀት በማዘጋጀት ለከንቲባው/ለካቢኔ ያቀርባል፣ ሲጸድቅም በሕግ መሠረት ያስተዳድራል፤

፫. ባልተማከለ የበጀት አስተዳደር ሥርዓት መሠረት የክፍለ ከተማዎች የበጀት ድልድል ቀመር አዘጋጅቶ ያቀርባል፣ ሲጸድቀም ተግባራዊ ያደርጋል፣ ለክፍለ ከተማዎች የሚሰጠው የበጀት ድጎማ በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ ምርመራ ያደርጋል፤

፬. በገቢዎች ባለሥልጣን የሚሰበሰበው ንዲሁም በብድርና በስጦ የሚገኘውን ገቢ፤ የከተማውን አስተዳደር ገንዘብ፣ የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ ብድርና የተለያዩ ፈንዶች ይጠብቃል፣ ያስተዳድራል፤ በአግባቡ ሥራ ላይ መዋላቸዉን ያረጋግጣል፤

፭. አዳዲስ የግብር ና የ ሪፍ ማሻሻያ ጥናቶች በማዘጋጀት የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፣ ሲጸድቅም ተገቢውን ይፈጽማል፤

፮. አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ከሀገር ዉስጥ ምንጮች በከተማው አስተዳደር ስም ይበደራል፤

፯. የቴክኒክ፣ የማቴሪያልና የገንዘብ ድጋፍ ከከተሞች ከዕርዳ ሰጪ አገሮችና ድርጅቶች ያፈላልጋል፤

፰. የከተማውን አጠቃላይ የሂሳብ አያያዝ ይመሰር ል፣ የሂሳብ ደረሰኞችን፣ ቅጾችንና መዛግብቶችን አሳትሞ ለማዕከል መሥሪያ ቤቶችና ለክፍለ ከተማዎች ያሰራጫል፤ አጠቃላይ የፋይናንስ ሪፖርት ያቀርባል፤

፱. አጠቃላይ የማህበረ-ኢኮኖሚ ችግሮችን ለመፍ ት የግሉን ክፍለ ኢኮኖሚ ተሳትፎ የሚያበረ የከተማውን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የልማት ስልቶች ያዘጋጃል ሲፈቀድም አፈጻጸሙን ይከ ተላል::

2. prepare and submit to the Mayor/Cabinet a consolidated annual budget or supplementary budget, as may be necessary, upon analyzing recurrent budget proposal received from the City Government organs and budgetary allocation of Sub-Cities and administer same in accordance with the law upon approval ;

3. prepare and submit budgetary allocation formula of sub-cities based on the decentralization principle of budget administration, implement same upon approval; inspect the expenditure of budget subsidy allocated to sub-cities;

4. custody the income collected by Revenues Authority from donation and loan; safeguard and administer the City Government's finance, local and external loans and various funds; ensure that they are properly utilized;

5. submit recommendations of new revisions on taxation and tariffs, implement same upon approval;

6. borrow money in the name of the City Government from internal sources in accordance with the appropriate law;

7. search for technical, material and financial supports from cities, donor countries and organizations;

8. establish general accounting systems of the City Government, publish and distribute financial receipts, formats and registers to the central organs of the Government and Sub-Cities; submit consolidated financial report;

9. prepare the socio-economic development strategy of the City that motivates the participation of the private sector to solve the overall socio-economic problems of the City; implement same upon approval;

፲. የከተማውን የኢኮኖሚ አካውንት፣ የኢንቨስትመንት ኘሮግራም ና የመንግሥት ወጪ ኘሮግራም በማዘጋጀት ያቀርባል፤

፲፩. የካፒ ል ኘሮጀክትቶች ከአጠቃላይ ኘላን ጋር መጣጣሙን ያረጋግጣል፣ የዕቅድ አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ያደርጋል፤

፲፪. ብሔራዊ የሥነ ሕዝብ ፖሊሲዎች ከከተማው ተጨባጭ ሁኔ ጋር በተገናዘበ መልኩ ሥራ ላይ ንዲውሉ ያደርጋል፤

፲፫. በፖሊሲ ጉዳዮች ጥናትና ምርምር በማካሄድ ለፖሊሲ ውሳኔ የሚረዱ ሃሳቦችን ያቀርባል፤

፲፬ ከከተማዉ አጠቃላይ ሀብት ጋር የተጣጣመ የረጅም፣ የመካከለኛና የአጭር ጊዜ ዕቅድ በከተማ ደረጃ በማዘጋጀት የዉሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፣ ሲጸድቅም አፈጻጸሙን በመከታተልና በመገምገም ሪፖርት ያቀርባል፤

፲፭. መንግሥ ዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በበላይነት ይመራል፤ ያስተባብራል፤ የልማት ፕሮግራሞች ወይም ፕሮጀክቶችን ዕቅድ ተቀብሎ ያበለፅጋል፣ ያፀድቃል፣ ድጋፍ ይሰጣል፣ አፈጻጸሙንም ከመንግሥት የትኩረት አቅጣጫ አንጻር መሆኑን በመከታተልና በመገምገም ሪፖርት ያቀርባል፤

፲፮. መንግሥ ዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሚያቀርቧቸው ኘ ሮጀክቶች አግባብነት በማረጋገጥ ስምምነቶችን ይመሰር ል፤ አፈጻጸማቸዉን ይከ ተላል፤

፲፯ የከተማዉን አስተዳደር ዓመታዊ ሒሳብ አጠቃሎ ይይዛል፤ በዋና ኦዲተር ያስመረምራል፤

፲፰ በመንግሥት ግዢና ንብረት አስተዳደር ፖሊሲዎች፣ መርሆዎችና አፈጻጸሞች ይከታተላል አስተዳደሩንም ያማክራል፤ ለአስተዳደሩ መሥሪያ ቤቶች የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፤

10. prepare and submit the economic account of the City, investment program and government expenditure program;

11. ensure that capital projects are in conformity with the general plan, cause monitoring and evaluation of the implementation of plans;

12. cause the implementation of National Population Policy in compliance with the existing realities of the City;

13. undertake research and studies on policy matters and submit policy proposals for decisions.

14. prepare and submit recommendation upon the long, medium and short term plan compatible to the general resource capacity of the City; up on approval of same, submit report of execution by follow up and evaluation;

15. direct and coordinate non-governmental organizations; accept, appraise and approve their program or project plans, provide support; submit report byfollowing up and evaluating that such plan is executed in accordance with priority concerns of Government;

16. conclude agreements and follow up the implementation of projects proposed by Non-Governmental Organizations in ascertaining their appropriateness;

17. keep the consolidated annual account of the City Government; cause it examined by the General Auditor;

18. follow up and advise the City Government on Government procurement and property administration policies, principles, and execution; provide technical support to the offices of the City Government on such issues.

፲፱ የመንግሥት ሀብትና ንብረት በአግባቡ ተጠብቆ ሥራ ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ የዉስጥ ኦዲት በሴክተር መሥሪያ ቤቶች፣ በክፍለ ከተሞችና በወረዳ እንዲቋቋሙ ያደርጋል፣ አፈጻጸማቸዉን ይከታተላል፣ የሙያ ድጋፍና ሥልጠና በመስጠት ዘመናዊ የዉስጥ ኦዲት አሠራር ሥርዓት እንዲሰፍን ያደርጋል፤

፳ የዉስጥ ኦዲት መመሪያዎች፣ ማኑዋሎችና የሙያ ሥነ ምግባር ደንብ በማዘጋጀት ሥራ ላይ እንዲዉልም ያደርጋል፤ የኦዲት ሪፖርቶችን ተቀብሎ ይገመግማል፤ የተገኙ ድክመቶች እንዲታረሙ ተገቢዉን ክትትል በማድረግ የመንግሥት ሀብትና ንብረት እንዲጠበቅ ያደርጋል፡፡

## ዘርፍ አሥራ ሁለት
## የጤና ቢሮና የሚያስተባብረው አካል ስልጣንና ተግባር

**፴. የጤና ቢሮ**

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩ ል:-

፩ የሀገሪቱን የጤና ፖሊሲና ደረጃ በማገናዘብ የከተማውን የጤና አገልግሎት ደረጃ ያወጣል፣ ተግባራዊነቱን ያረጋግጣል፣ በጤና ጉዳዮች ላይ የግንዛቤ ማስፋፊያ ትምህርት ለከተማው ነዋሪ አመቺ በሆነ ዘዴ ይሰጣል ወይም ንዲሰጥ ያደርጋል፣

፪. አጠቃላይ የሆነ የተላላፊ በሽ ዎች ቁጥጥርና ቅኝት ያደርጋል፣ ይቆጣጠራል፣ ይከላከላል፣ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ወረርሽኝ ሲነሳ ከሚመለከ ቸው አካላት ጋር በመተባበር ይከላከላል፤

፫. የ ናቶችና ህጻናት ጤና ንክብከቤ አገልግሎት ይሰጣል ወይም ንዲሰጥ ያደርጋል፣ ይቆጣጠራል፤

፬. በአስተዳደሩ ባለቤትነት ሥር ያሉ ሆስፒ ሎችንና የሕክምና ማሰልጠኛ ተቋማትን በሕግ መሠረት ያስተዳድራል፤

19. Cause internal audit established within the sector offices, Sub-Cities, and wereda with the view to ensure that government resource and property is properly kept and used; follow up their execution; cause modern internal audit procedure implemented by providing professional support and training;

20. Prepare and implement internal audit directives, manuals and code of ethics; accept and evaluate audit reports; cause errors be corrected through follow up and thereby government resource and property kept properly.

## *Section Tweelve*
## *Powers and Functions of the Health Bureau and Organs it Coordinates*

**30. Bureau of Health**

The Bureau shall have the following powers and functions to:

1. establish health service standards and ensure its implementation in accordance with the National Health Policy and Standards; provide or cause to be provide health awareness raising education to the residents of the City;
2. control, conduct surveillance, supervise, prevent and collect information concerning communicable disease upon conducting survey and investigation; prevent epidemic diseases in collaboration with appropriate organs;
3. provide or cause the provision of mothers and children health care service and supervise the same;
4. administer, in accordance with the law, hospitals and health care training institutions owned by the City Government;

፭. ከፌዴራል መንግሥት ና ከዕርዳ ሰጭ ድርጅቶች ለተለያዩ ፕሮግራሞች ማስፈጸሚያ የሚሰጡ መድ ኒቶችንና የሕክምና መሳሪያዎችን ያሰራጫል፤

፮. የባህል ሕክምና ከዘመናዊ ሕክምና ጎን ተጠናክሮ የሚሄድበትን ሥልት ይቀይሳል፤

፯. የጤና አገልግሎት ፕሮግራሞችን ከሚያካሂዱ መንግሥ ዊ ያልሆኑ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ጋር ስምምነቶችና ውሎች ይፈጽማል፤ አፈጻጸማቸውን ይከ ተላል፣

፰ በከተማው ውስጥ የሚከናወኑ የኤች.አይ.ቪ. /ኤድስና ሌሎች በሽ ዎች ቁጥጥር መረጃ ያጠናቅራል፣ በአግባቡ በመተንተን ለሚመለከ ቸው ያቀርባል፤

፱ የጤና አጠባበቅ የምክርና የመረጃ አገልግሎት ያደራጃል፣ ይሰጣል::

፲ መንግስ ዊ ጤና ተቋሚት የሚሰጡትን የሕክምና መረጃዎች ያረጋግጣል፣ ይከ ተላል፣ ንደ አስፈላጊነቱም ርምጃ ይወስዳል::

## ፴፩ የኤችአይ ቪ/ ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት

የኤች.አይ.ቪ.ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፲፩/፲፱፻፺፭ የተደነገገው ስልጣንና ተግባር፣ ንዲሁም አደረጃጀትና አሰራር ይኖረዋል::

## ዘርፍ አሥራ ሦስት
## የፍትሕ ቢሮና የሚያስተባብራቸው አስፈጻሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር

## ፴፪. የፍትሕ ቢሮ

ቢሮው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩ ል፡-

፩ የደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽሕፈት ቤትን፣ ና የማህበራዊ ፍርድ ቤቶች የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ጽህፈት ቤትን በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ንዲሁም የፍትህ ስርአት ማሻሻያ ፕሮግራምን ይፈጽማል፣ በ ነዚህና በሌሎች የአስተዳደሩ የፍትሕ አካላት መፈጸሙን ያረጋግጣል፤

5. distribute medicens and medical equipments that are provided by the Federal Government and donor organizations for the implementation of different programs;
6. develop strategies for the application of traditional medicens and treatment together with modern/contemporary medicens;
7. conclude agreements and contracts and sign agreements with Non-Governmental charity organizations that conduct programs of medical services and follow up the implementation of same;
8. organize data on the activities undertaken to control and prevent H.I.V/AIDS and other diseases in the City, submit the results of the analysis of the data to the appropriate organs;
9. organize and provide health care counseling and information services.
10. ensure medical information given by government health institutions, follow up, and take measures where necessary.

## 31. H.I.V/AIDS Prevention and Control Office

The Office shall have the powers and functions as well as organization structure and operation defined in Proclamation No.11/2003 of the Addis Ababa City Government.

## *Section Thirteen*
## *Powers and Functions of Bureau of Justice and Other Executive Organs it Coordinates*

## 32. Bureau of Justice

The Bureau shall have the following powers and functions:

1. direct and coordinate the Office of the Code Enforcement Service, and Judicial Administration Council Office of the Social Courts; implement the justice reform program and ensure implementation of same by these and other justice organs of the City Government.

፪ በሕግ ጉዳዮች የከተማው አስተዳደር ዋና የህግ አማካሪ ሆኖ ይሠራል፤ በቢሮዎች፣ በሌሎች አስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት ሲጠየቅ የሕግ ምክር ይሰጣል፤

፫ የአስተዳደሩን ና የነዋሪዎችን መብትና ጥቅም ለማስከበር አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በፍርድ ቤት ና በማናቸውም የዳኝነት ስልጣን በተሰጠው አካል ወይም በግልግል ጉባዔ ክስ ይመሠር ል፣ ክስ ንዲመሠረት ያደርጋል፣ ወይም በህግ መሠረት ጣልቃ በመግባት ወይም መቃወሚያ በማቅረብ ይከራከራል፤

፬ በካቢኔው በሚፀድቅ ወይም በፀደቀ መዋቅራዊ አደረጃጀት መሠረት የ ራሳቸው የሕግ አገልግሎት ንዲኖራቸው ከተፈቀደላቸው አካላት በስተቀር ቢሮዎች፣ የከንቲባው ጽህፈት ቤትንና የከተማው ሥራ አስኪያጅ ጽህፈት ቤትን ጨምሮ ሌሎች አስፈጻሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት ሲከሰሱ ወይም ሲከሱ በዳኝነት አካላት ፊት ወክሏቸው በየስማቸው በሕግ መሠረት ይከራከራል፣ የማያዋጡ ክርክሮች ንዳይካሄዱ ወይም ንዲቋረጡ ያደርጋል፣ የ ራሳቸው የሕግ አገልግሎት ንዲኖራቸው በካቢኔው የተፈቀደላቸው ሌሎች የከተማው አስተዳደር አካላት ተከራካሪ የሆኑባቸውን የፍትሐብሔር ክርክሮችና የመብት ጥያቄዎች አያያዝ ንደአስፈላጊነቱ ይከ ተላል፣ የማስተካከያ ርምጃዎችን ይወስዳል፣ ወቅ ዊ ሪፖርት ንዲቀርብለት ያደርጋል፣ ንዲሁም ለሕግ አገልግሎቶቹ ብቃት ያለው የሰው ይል የተመደበላቸው መሆኑን ያረጋግጣል፤

፭ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ንደተጠበቁ ሆኖ የክፍለ ከተማ ንዲሁም የወረዳ የፍትህ ጽህፈት ቤቶችን በሙያ ረገድ በበላይነት ይቆጣጠራል፣ ቢሮውም ሆነ ጽህፈት ቤቱ የህግ ባለሙያ ችግር ሲያጋጥማቸው ከአንድ ክፍለ ከተማ ወይም ወረዳ የፍትህ ጽህፈት ቤት ወደ ሌላ ክፍለ ከተማ የፍትህ ጽህፈት ቤት ወይም ወደ ቢሮ ወይም ከቢሮ ወደ ጽህፈት ቤት በዝውውር ወይም በደረጃ ድገት በመመደብ ለተፈጠረው ችግር መፍትሔ በመስጠት ንዲሰራ ያደርጋል፤

2. be chief advisor to the City Government on legal matters; provide legal advices to Bureau and other executive organs upon request;
3. institute, cause to institute or intervene in suits or present objection before courts and any adjudicating organ or arbitration commission whenever it deems necessary to protect the rights of the City Government and the interests of residents;
4. represent in litigations Bureaux, Office of the Mayor including Office of the General Manager, other executive and municipal organs with the exception of organs permitted to have their own legal service unit in accordance with organizational structure approved by the Cabinet; terminate non-viable litigations, follow up the handling of civil suits and claims in which organs of the City Government that are permitted to have their own legal service unit are a party as may be necessary; take corrective measures and request periodic reports; ensure that qualified personnel are assigned to such units;
5. without prejudice to the provisions of this proclamation, supervise Justice Offices of the Sub-Cities or wereda's on matters of profession; in cases of shortage of legal experts within the Bureau and the Offices, assign same through transfer or promotion from the Justice Offices of a Sub-City or Wereda to the other or to the Bureau or from the Bureau to the Offices for solving problems encountered;

፮ ከንቲባው ወይም የቢሮ ላፊዎች ከሌላ ወገን ጋር የሚያደርጓቸውን ስምምነቶችና ውሎች ሲጠየቅ ያዘጋጃል፤

፯ አዳዲስ ሕጎች ንዲወጡ ሃሳብ ያመነጫል፣ በነባር ሕጎች ላይ ጥናትና ምርምር በማድረግ የማሻሻያ ሃሳቦችን ያቀርባል፣ ንዲሁም ከሌሎች ቢሮዎች፣ የሙያና የብዙ ን ማኀበራት አዲስ ሕግ ንዲወጣ ጥያቄ ሲቀርብ ንደየአግባቡ ጥናት ያደርጋል፣ የሕግ ረቂቅ በማዘጋጀት ያቀርባል፤

፰ የሕግ ምርምርና ጥናት ያካሂዳል፣ የከተማውን ነዋሪና የሚያስተባብራቸውን አካላት ባልደረቦችን ንቃተ-ሕግ ለማዳበር የሕግ ትምህርትና ስልጠና ይሰጣል፣ የሕግ ትምህርትና ሥልጠናን በተመለከተ አግባብ ካላቸው አካላት ጋር ይተባበራል፤ የአስተዳደሩን ሕጎች በማሰባሰብ ለጥናትና ለምርምር ሥራ በሚያመች መንገድ ያደራጃል፣ የአስተዳደሩን ሕጎች የማሰባሰብና የማሰራጨት ሥራ ያከናዉናል፣

፱ በከተማዉ በተለያዩ ሀይማኖቶችና እምነቶች ተከታዮች መካከል ሠላምና መከባበር እንዲሰፍን ለማድረግና ግጭትንም ለመከላከል እንዲቻል አግባብነት ካላቸዉ የፌደራልም ሆነ የከተማዉ አስተዳደር መንግሥት አካላት፣ የኃይማኖት ተቋማትና ከሌሎች ማናቸዉም አካላት ጋር በመተባበር ይሠራል::

## ፴፫. የደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽህፈት ቤት

ጽህፈት ቤቱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩ ል:-

፩ የደንብ ማስከበርን የሚመለከቱ ሕጎችና ደንቦች በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከ ተላል፤ ሕገወጥነትን ይከላከላል፤

፪ የጽዳት መጓደል፣ ሕገ-ወጥ ንግድ፣ ሕገ-ወጥ ግንባ ና ሌሎች ደንብ መተላለፍን ይቆጣጠራል፣ በሕግ መሠረት ተገቢው ርምጃ ይወሰዳል ወይም ንዲወሰድባቸው ያደርጋል፤

፫ የከተማን ደንብ ከማስከበር ጋር በተያያዘ በተለያዩ መንግሥ ዊ አካላት፣ ማሕበራትና ድርጅቶች ሲጠየቅ ድጋፍ ያደርጋል፣ ንዳስፈላጊነቱም ሥልጠና ይሰጣል፤

6. prepare, upon request, agreements and contracts in which the Mayor or Bureau Heads are involved with other parties;
7. initiate new laws, amendments of laws based on research and studies, conduct studies for the enactment of new laws upon the request of Bureaux, professionals and civil associations; prepare and submit draft laws;
8. Conduct legal research and studies; provide legal education to raise the legal conciousness of the residents; cooperate with the appropriate organs on legal education and training; organize the laws of the City Government in a way comfortable for research and studies; compile and distribute the laws of the City;
9. Work in collaboration with pertinent Federal as well as the City Government organs, religious institutions and other organs to ensure that peace and mutual respect will prevail among followers of different religions and beliefs, and to be able to prevent conflicts within the City.

## 33. Office of the Code Enforcement Service

The Office shall have the following powers and functions :

1. follow up the implementation of laws and regulations regarding code enforcement; prevent illegality;
2. control non-hygienic, illicit trade, unauthorized construction and other violation of laws; take or cause to be taken legal measures on same;
3. render support upon request, to Governmental organs, associations and organizations operating in connection with code enforcement in the City, give training as may be necessary;

፬ የከተማው ነዋሪ የከተማው የደንብ ማስከበር አገልግሎት የሥራ ክንውንን በተመለከተ ወቅ ዊ መረጃ የሚያገኙበትን ሁኔ ያመቻቻል፣ የከተማው ነዋሪዎች ለአገልግሎቱ መጠናከር ተገቢውን ድጋፍ ሊያደርግ የሚችልበትን ሁኔ ከሚመለከ ቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ይሰራል፣

፭ የጽህፈት ቤቱ ዝርዝር አደረጃጀትና አቋም በካቢኔ በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

## ፴፬. የማህበራዊ ፍርድ ቤቶች የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ጽህፈት ቤት

ጽህፈት ቤቱ በዚህ አዋጅ የተደነገገው ንደተጠበቀ ሆኖ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የማህበራዊ ፍርድ ቤቶች የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፴፩/፲፱፻፺፱ የተደነገገው ስልጣንና ተግባር፣ ንዲሁም አደረጃጀትና አሰራር ይኖረዋል፡፡

## ዘርፍ አሥራ አራት
## የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ቢሮና የሚያስተባብራቸዉ አስፈፃሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር

## ፴፭ የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ቢሮ

ቢሮው በምክትል ከንቲባ ደረጃ በሚሾም ሀላፊ የሚመራ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩ እያንዳንዱ ቢሮ ተጠሪነቱ ለከንቲባዉ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ለከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፍ ፖሊሲ ትግበራና ቅንጅት ሲባል የኮንስትራክሽንና ቤቶች ልማት ቢሮን፣ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮን፣ የመንገድና ትራንስፖርት ቢሮንና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላትን ያስተባብራል፣ ያቀናጃል፣

4. facilitate ways by which residents of the City will have access to up to date information on the activities of the Code Enforcement Services of the City; work in collaboration with concerned organs on the ways of obtaining the support of the City residents to strengthen the service;

5. Details about organization and structure of the Office shall be determined by regulation issued by the Cabinet.

## 34. Office of the Judicial Administration Council of the Social Courts

Without prejudice to the provisions of this Proclamation, the Office shall have the powers and functions as well as organization structure and operation stated under the Addis Ababa Judicial Administration of the Social Courts Establishment Proclamation No.31 of 2007.

## *Section Fourteen*
## *Power and Functions of Land Development and Management Bureau and Executive Organs it Coordinates*

## 35. Land Development and Management Bureau

The Bureau, being headed by official appointed at the level of deputy mayor, shall have the following powers and functions:-

1. without prejudice to that each Bureau is accountable to the Mayor, cooperate and coordinate Bureau of Construction and Housing Development, Bureau of Micro and Small Scale Enterprises Development, Bureau of Road and Transport, and Municipal Service Organs for the purpose of implementation and coordination of the urban development and construction policy;

፪ የመሬት ልማትና ከተማ ማደስ ኤጀንሲን፣ የመሬት ባንክና ማስተላለፍ ጽህፈት ቤትን፣ የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣንን፣ የከተማ ፕላን ኢንስቲቲዩት፤ የመሬት መረጃና ቴክኖሎጂ ማዕከልን፤ የተቀናጀ የመሬት መረጃ ሥርዓት ዝርጋታ ፕሮጀክት ማስተባበርያ ጽህፈት ቤትን፤ የማይንቀሳቀስ ንብረት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲን፣ የይዞታ አስተዳደር የሽግግር ጊዜ አገልግሎት ፕሮጀክት ጽህፈት ቤትን በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል ያቀናጃል፣

፫ ስለከተማው ቦታዎች የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች አመዘጋገብና መረጃ አያያዝ የወጡ ፖሊሲዎችና ሕጎች መፈፀማቸውን ይከታተላል ከሕግ ውጪ በሚሰሩ የቦታ ማስተላለፎች ፤መረጃ አያያዞች ላይ እርምጃ ይወስዳል፤ ያስወስዳል፣

፬ ከተማዋ በፕላን እድትመራ የከተማው የመሬት አጠቃቀምና ግንባታ አፈፃፀም የወጡ ፕላኖችን የተከተሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣

፭ በከተማዋ የመሬት አቅርቦቱና ፍላጎቱ ሚዛኑን ጠብቆ መሄድ እንዲችል የተለያዩ ጥናቶችን በማከናወን የመፍትሄ እርምጃዎችን ይወስዳል፣

፮ የመሬት ልማትና ማኔጅመንት አፈፃፀምና መሬት ለተጠቃሚዎች የሚፈቀድባቸው ሥርዓቶች የሚመሩባቸውን የአገልግሎት አሰጣጥ መመሪያዎች በጥናት ወቅታዊ ያደርጋል ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፣

፯ የመሬትና የከተማ ልማት ማምጣት የሚያስችል የህብረተሰብ ተሳትፎ በየአካባቢው እንዲደራጅ ድጋፍ ያደርጋል፣

፰ ቢሮው የታችኛውን የአስተዳደር መዋቅር የግምገማ ውጤት ወስዶና ከተጨባጩና ለስራው ካለው ፋይዳ ጋር መዝኖ እርምጃ ይወስዳል፤ ያስወስዳል ለሚመለከታቸው አካላት ያሳውቃል፣

2. superiorly direct, coordinate and integrate the Land Development and City Renewal Agency, Land Bank and Transfer Office, Building Permit and Control Authority, Urban Plan Institute, Land Information and Technology Centre, Integrated Land Information System Installation Project Coordination Office, Immovable Property Registration and Information Agency, Title Administration Transitional Period Service Project Office;
3. follow up proper implementation of the registration and keeping date of land improvable properties of the city based measures. Cause however to be taken where execution of transfers and keeping data country to law.
4. install a system which ensures the land use and construction in the city accordance with the plans issued.
5. conduct studies and take measures to strike the balance between the demand and supply of land within the City.
6. make update, by conducting study development directives of service delivery by which land and administration execution and produces of permitting land to the users is regulated and follow up its execution.
7. provide support for the organization of public participation at areas of the City to create society based land and city development;
8. take corrective measure or cause measures to be taken and inform for appropriate bodies, after receiving evaluation results from the lower structure by relation it with its purposes with the task;

፱ እስከታችኛው መጨረሻ እርክን የሚኖረውን ቢሮውን የሚመለከቱ ቀን ተቀን ቴክኒካዊ ውሳኔ የሚሻን ጉዳዮች ይወስናል ይተገብራል፤ እንዲወሰን ያደርጋል ያስተገብራ ይከታታላል ይቆጣጠራል፣

፲ የቻርተሩና የዚህ አዋጅ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በመሬት ልማት ተቋማት መካከል የባለሙያ እጥረት ሲፈጠር ከአንዱ ተቋም ወደ ሌላው ተቋም ወይም ወደ ቢሮው በጊዜያዊነት ወይም በዝውውር ወይም በደረጃ ዕድገት በመመደብ ለተፈጠረው ችግር መፍትሔ በመስጠት እንዲሰራ ያደርጋል፡፡

9. decide cause to he decides issues which needs day to day technical decisions which extends to last structure,abd implement, cause to be implemented by same;
10. assign through transfer or promotion in cases of shortage of legal experts within the land development institutions, assign same through transfer or promotion from one institution to other or to the Bureau.

**፴፮ የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን፤**

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

፩ መሬት የተፈቀደላቸው አልሚዎች ወይም ህጋዊ የመሬት ባለይዞታዎች በከተማው መዋቅራዊና በአካባቢ የልማት ፕላኖች እንዲሁም የግንባታ ደረጃ መሰረት እንዲገነቡ የፕላን ስምምነት መረጃ ይሰጣል፣

፪ የፕላን ስምምነት የተሰጣቸው አልሚዎች ወይም ህጋዊ የመሬት ባለይዞታዎች በከተማው መዋቅራዊና በአካባቢ የልማት ፕላኖች እንዲሁም የግንባታ ደረጃና ህግ የሚፈልገውን አሟልተው የሚቀርቡለትን የግንባታ ዲዛይኖች አግባብነት ባለው ህግ መሠረት መርምሮ ያፀድቃል የግንባታ ፈቃድ ይሰጣል፣ በጸደቀዉ ዲዛይንና በተሰጠዉ የግንባታ ፈቃድ መሠረት መገንባታቸዉን ይቆጣጠራል፣

፫ የግንባታ ማሻሻያና የእድሳት ጥያቄዎችን በተመለከተ አግባብ ባለው ህግ መሠረት መርምሮ ፈቃድ ይሰጣል፣

**36. Building Permit and Control Authority:-**

The Authority shall have the following powers and functions:-

1. issue plan agreement document to developers to whom land has been allocated or legal possessors of land to build in accordance with the structural and local development plans as well as levels of construction;
2. investigate and approve construction designs, which are presented by developers or legal possessors of land to whom plan agreement has been issued after fulfillment of requirements provided for the structural and local development plans as well as construction level and law, on the basis of appropriate law; issue building permit to same; control that the construction is in accordance with the approved design and issued building permit;
3. investigate into and issue license regarding matters of renewal and improvement of construction based on appropriate law;

፬ በግንባታ ቦታዎች የሚቀርቡ ግብአቶች በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማትና ቁጥጥር ባለሥልጣን በተረጋገጠዉ ጥራት መሠረት መሆኑን ያረጋግጣል፣ የጥራት ጉደለት አለበት ብሎ ያመነበትን በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማትና ቁጥጥር ባለሥልጣን በኩል እንዲረጋገጥ ያደርጋል፣

፭ በከተማው አስተዳደር የሚገኙ ግንባታዎችን በተመለከተ የተሟላ መረጃ ይይዛል ወቅታዊ ያደርጋል መረጃዎችን ያሰራጫል፣

፮ በከተማዋ ክልል ውስጥ ለሚተከሉና በከተማ ውስጥ ባሉ ህንፃዎች ላይ ለሚለጠፉ የማስታወቂያ ሰሌዳዎች የሚመለከታቸውን አካላት በማሳተፍ ስታንዳርድ ያወጣል፤

፯ ከተማዋ ክልል ውስጥ ለሚተከሉና በከተማ ውስጥ ባሉ ህንፃዎች ላይ ለሚለጠፉ የማስታወቂያ ሰሌዳዎች በጠየቁት ቦታ ላይ ለመትከል ወይምለመለጠፍ ህጋዊ መብት ያላቸው መሆኑን በማረጋገጥ በህግና እስታንዳርዱ መሠረት መርምሮ ፈቃድ ይሰጣል፤ በተፈቀደላቸው መሠረት መተከላቸውንና መለጠፋቸውን ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፣

፰ የግንባታ ቅንጅት ለማጎልበት የሚያስችል ጥናት ያካሂዳል ገንቢዎች ሥራዎችን አቀናጅተው እንዲሰሩ ያደርጋል፣

፱ የከተማው የመሰረተ ልማት ሥራዎች እንዲጣጣሙ የከተማዋን መዋቅራዊ ፕላንና ስታንዳርዶች መሠረት አድርጎ የተቀናጀና ደረጃውን የጠበቀ ዝርዝር የኔትወርክ ፕላን ያዘጋጃል፤ ሲፈቀድም ለትግበራ ያስተላልፋል ፣

4. ascertain that quality of construction materials supplied to construction sites is up to the quality set by the Construction Industry Development and Control Authority; cause the confirmation by the Construction Industry Development and Control Authority the quality of those it finds deficient in quality;
5. keep fulfilled data regarding constructions within the City Government; update and disseminate same;
6. set standard, in consultation with the concerned bodies, for advertisement boards erected within the boundary of the City and posted on buildings within the City;
7. issue license in accordance with the law and standard, upon assuring that there is legal right to do so, for advertisement boards erected within boundary of the City and posted on buildings in the City; follow up and control that same is erected or posted in accordance with the permit;
8. conduct research that enables strengthening coordination of construction; cause the constructors perform their activities in a coordinated manner;
9. prepare coordinated and standardized detailed network plan based on the structural plan and standards of the City with the view to harmonize the infrastructure work of the City; transfer same for implementation upon approval;

፲ የመሰረተ ልማት ዘርጊዎች አዲስ ለሚሰሩትም ሆነ ከድንገተኛ ጥገና ዉጭ ለሚያከናውኑት የመሰረተ ልማት ጥገና፤ እድሳትና መሻሻል ዝርዝር ዲዛይንና የግንባታ መርሃግብር እንዲያቀርቡ ያደርጋል፣ መርምሮ አቀናጅቶ ፈቃድ ይሰጣል፣ በፈቃዱ መሠረት መፈጸሙን ይከታተላል ይቆጣጠራል፣ ከፈቃድ ውጭ ሆኖ ካገኘ እርምጃ ይወስዳል፣

፴፯. የመሬት ልማትና ከተማ ማደስ ኤጀንሲ

ኤጀንሲዉ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤-

፩ የከተማውን የመሬት ልማት እና ከተማ ማደስ አፈፃፀም ስትራቴጂዎችን ነድፎ ያቀርባል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፣

፪ የከተማውን መሪና መዋቅራዊ ፕላን እና የአካባቢ ልማት ዝርዝር ፕላኖችን መሠረት በማድረግ የመሬት ልማትና የከተማ ማደስ ጥናት ሥራ ያከናውናል፣

፫ በከተማዋ ክልል ውስጥ ለተለያዩ የልማት ሥራዎች የሚውል መሬት ያዘጋጃል፣

፬ በህዝብ ተሣትፎ የሚለማው እንደተጠበቀ ሆኖ የከተማዋ የተጎዱና የደቀቁ አካባቢዎችን በመልሶ ማልማት ሥራ ያለማል፤ ያድሳል፣

፭ ከተማው ውስጥ በልዩ ልዩ የልማት ሥራዎችና መልሶ ማልማት ተነሺ ለሆኑት ተገቢውን የካሳ ግምት ይተምናል፤ የካሣ ክፍያ ይፈፅማል፤ ምትክ ቦታ እና የምትክ ቤት መቀበያ ሰርተፊኬት ይሰጣል፤አፈፃፀሙን ይከታተላል፣

፮ በከተማው ውስጥ ለሚዘረጉ የመሠረተ ልማት አውታሮች፤ ለልዩ ልዩ አገልገሎቶች ለመናፈሻ ቦታዎች አረንጓዴ ቦታዎች እንዲሁም ለሕዝብ መሰብሰቢያ ፕላዛዎች በፕላኑ መሠረት ወሰናቸውን ይከታተላል፣ የወሰን ማስከበር ሥራዎች ያከናውናል፣ የይዞታ የምስክር ወረቀት እንደየአግባቡ እንዲሰጥ ለሚመለከተው አካል ያስተላልፋል፤



10. cause the infrastructure developers submit detailed design and construction schedule regarding new constructions as well as repair, renewal and improvement with the exception of emergency repair works; issue license upon investigation and coordination; follow up and control that the work is done in accordance with the license; take measure if the work is done contrary to the license issued;

**37. Land Development and City Renewal Agency**

The Agency shall have the following powers and functions:-

1. design and submit execution strategies of land development and city renewal; implement same upon approval;
2. conduct study works on land development and city renewal based on the master and structural plan as well as specific local development plans;
3. prepare land to be used for different development works within the City;
4. notwithstanding those to be developed through public participation, develop and renew, through renewal works, areas of the City which are damaged and deteriorated;
5. fix and effect the proper compensation payment to persons displaced due to different development and renewal works in the City; issue certificate of substitute plot and house receiving certificate; and follow up the execution thereof;
6. follow up boundary, based on the plan, of development infrastructures, different services like recreation areas, green areas and even public gathering plazas in the City; undertake boundary preservation works; transfer to the concerned bodies for the issue of certificate of possession, as may be proper;

፯. የማዕድን ማውጫ ቦታዎችን የከርሰ መሬት ጠቀሜታ ለሚውሉ የድንጋይ የጠጠር እና የገረጋንቲ ቦታዎች በፕላኑ መሠረት ከልሎ በማስቀመጥ ለመሬት ባንክና ማስተላለፍ ጽህፈት ቤት ያስረክባል፤ የቦታዎቹ ጠቀሜታ ሲያበቃም ተከታትሎ በመረከብ እና በማደስ ለዳግም ልማት ያዘጋጃል፤

፰. ለግንባታ ተረፈ ምርት መድፍያነት አገልግሎት የሚሰጡ ቦታዎችን ከልሎ ለግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን ያሳውቃል፤ ያስተዳድራል፣ በግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን በተሰጠዉ ፈቃድ መሠረት በተገቢው የተደፋ መሆኑን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

፱. አግባብነት ባለዉ ህግ መሠረት የከተማ ቦታ የማስለቀቅ ትዕዛዝ ይሰጣል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

፲. ለተነሺዎች ምትክ ቦታ ያዘጋጃል፤ የምትክ ቤት ፍላጎትን ያጠናል፡ ለሚመለከተዉ ያሳዉቃል፤ ሲፈቀድም ለተነሺዎቹ ምትክ ቦታና ቤት ድልድል ያደርጋል፤

፲፩. በመልሶ ማልማትና ለመሬት ዝግጅት ተፈላጊዉን መሠረተ ልማት ያጠናል፤ ለሚመለከታቸዉ ያሳዉቃል፤ ከገንቢዎች በሚገኝ ግብአት የግንባታ ቅንጅት ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፤ ሲፈቀድም ያስገነባል፤

፲፪. ለከተማዋ ልማት የሚበጅ ሆኖ ሲያገኘዉ አስተዳደሩን በማስፈቀድ ከአገር ዉስጥ ምንጭ ይበደራል፤ የመሬትን የሊዝ ሒሳብ በማስላት ከሌሎች የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ወይም የግል አልሚዎች ጋር በሽርክና ኢንቨስት ያደርጋል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ድርሻዉን ያስተላልፋል፤

7. transfer on lease basis to temporary users based on the license issued by the Environmental Protection Authority of the City to exploit underground minerals of stone, gravel, and selected material areas by demarcating according to the plan; where use of such places comes to an end, it recovers to renew and prepare for another development activity;
8. demarcate, administer and notify to the Building Permit and Control Authority areas serving for depositing waste materials of construction; control and follow up that waste materials are deposited in appropriate manner according to the license issued by the Building Permit and Control Authority;
9. give order for land clearance in accordance with appropriate law; follow up the implementation thereof;
10. prepare substitute plot of land for displaced persons; study the demand for substitute house; notify to the concerned body; allocate substitute plot of land and house to the displaced upon permission;
11. study the necessary infrastructure for renewal and land preparation; notify to the concerned bodies; prepare construction coordination plan and budget based on the feedback found from builders; cause built upon permission;
12. get a loan from domestic source upon permission of the City Government where it finds proper for development of the City; invest in partnership along with other public enterprises or private developers by contributing the lease price of land; transfer its share where it is found necessary;

## ፴፰. የመሬት ባንክና ማስተላለፍ ጽህፈት ቤት

ጽህፈት ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩ ለህዝብ ጥቅም እንዲውሉ በተፈለጉ ቦታዎች እና መልሰው በሚለሙ አካባቢዎች ላይ የሚገኙ ንብረቶችና ይዞታዎች ካሳ ጥናትና ግመታ ያከናውናል፤ ተገቢው ስለመፈፀሙም ያረጋግጣል፤

፪ በካርታ በተደገፈ መልኩ የከተማ ቦታ ደረጃ እና የሊዝ መነሻ ዋጋ ጥናት ያካሂዳል፣ ለከተማዉ አስተዳደር ካቢኔ አቅርቦ ያጸድቃል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣ ይህን አስመልክቶ የሚወጡ ወቅታዊ መረጃዎችን ለኅብረተሰቡ ያሰራጫል፤

፫ በይዞታነት ለማንም አካል ያልተላለፉ የተዘጋጁና ያልተዘጋጁ ቦታዎችን ይከልላል፣ በዲጂታል እና በፕላን ፎርማት ተገቢውን መረጃ ይይዛል የቦታውንም አገልግሎት ደረጃ እና አስፈላጊ መግለጫዎችን የያዘ የመለያ ሰሌዳ ይተክላል፣ ቦታዎቹ ለህገወጥነት እንዳይጋለጡ ይከላከላል ህገወጥነት ተፈፅሞ ሲገኝም ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፣

፬ የማዕድን ማውጫ ቦታዎችን የከርሰ መሬት ጠቀሜታ ለሚውሉ የድንጋይ የጠጠር እና የገረጋንቲ ቦታዎችን ከከተማዉ አካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን በሚሰጥ የማዕድን ማዉጫ ፈቃድ መሠረት በጊዜያዊነት ለሚጠቀሙ መሬቱን በሊዝ ያስተላልፋል፤

፭ በማስፋፊያ እና በመልሶ ማደስ አካባቢዎች ለልዩ ልዩ የልማት ሥራዎች የለማ መሬትን በባንኩ በመመዝገብ ወጥ የሽንሻኖ ቁጥር በመስጠት ጨረታ ያወጣል፤ ለአሸናፊዎች ቦታውን በመስክ ያስተላልፋል፣ ቦታው ለተጠቃሚ እስከሚተላለፍ ድረስም የመከላከልና የመጠበቁን ሥራ ያከናውናል፣

## 38. Land Bank and Transfer Office

The Office shall have the following powers and functions:-

1. conduct study on the compensation scheme of properties and possessions situated at places intended to be used for public purposes and renewal areas; valuate and ensure the proper execution thereof;

1. conduct study on urban land grade and lease initial price in a way supported by map; submit same to the Cabinet of the City Government for approval; implement same upon approval; disseminate current information thereof to the public;

2. demarcate plots of land that are prepared or otherwise but not possessed by anybody; keep proper information in digital and plan format; erect information board containing the service for which the land is to be used, the level and necessary descriptions; protect the land against illegal acts and take proper measures where an illegal act takes place;

3. transfer on lease basis to temporary users based on the license issued by the Environmental Protection Authority of the City to exploit underground minerals of stone, gravel, and selected material areas;

4. run auction of plots of land prepared for different development activities in expansion and renewal areas by registering in the bank and issuing uniform parcel number; transfer the plot of land in the field to the winners of the auction; perform protection and safeguarding activities until the land is transferred to the beneficiary;

5. transfer on temporary lease basis plots of land allocated to micro and small scale enterprise services, car washing services; prepare for another development activity by holding back and renewing the plot upon lapse of the contract period or service thereof;

፮ ለጊዜያዊ መጠቀሚያነት ለጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት አገልግሎት የሚሰጡ ቦታዎችን፣ ለመኪና ማቆሚያና ማጠቢያነት አገልገሎት የሚሰጡ ቦታዎችን በጊዜያዊ ሊዝ ያስተላልፋል፤ የውል ጊዝያቸው ወይም አገልገሎታቸው ሲያበቃም በመረከብ እና በማደስ ለዳግም ልማት ያዘጋጃል፣

፯ ለማናቸውም ግንባታ የሚውል ቦታ በሊዝ ሕግ መሠረት በጨረታ ወይንም በምደባ ያስተላልፋል፤ የሊዝ ውል ይዋዋላል፤ ቦታ ያስረክባል፤ በውል መሰረት የሊዝ ክፍያ ይሰበስባል፣

፰ በተፈረመው የሊዝ ውል መሠረት ግንባታ መከናወኑን ያረጋግጣል፤ በሕግና በውል በተወሰነው ጊዜና ሁኔታ ግንባታ ካልተጀመረ ወይም ካልተጠናቀቀ በሊዝ ሕግ መሠረት ተገቢውን ዕርምጃ ይወስዳል፣

፱ በከተማዉ ልማትን በአግባቡ ለማመጣጠን የመሬት አቅርቦትንና ፍላጎትን ይመራል፡፡

**፴፱ የይዞታ አስተዳደር የሽግግር ጊዜ አገልግሎት ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት**

የፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤-

፩ በውዝፍነት የሚታዩትንና ተለይተው የታቀዱትን ፕሮጀክቶች ያዋቅራል፣ያደራጃል፣

፪ ፕሮጀክቶቹ ሊመሩባቸውና ሊፈጽሟቸው የሚገቡ መነሻ የስራ ዕቅዶችን በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው አካላት አስፈላጊውን ማስገንዘቢያ በመስጠት ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፣ ይከታተላል፣

6. transfer land for any construction by tender or allotment in accordance with lease law; conclude lease contract; hand over the land, and collect lease payment based on the lease contract;
7. ensure that construction takes place in accordance with the lease contract; take appropriate measure in accordance with the lease law where the construction has not been commenced or accomplished in accordance with the time and condition provided by law and contract;
8. direct land supply and demand with the view to properly balance development of the City.

**39. Title Administration Transitional Period Service Project Office**

The project office shall have the following powers and functions:-

1. organize and structure the projects considered to be residual and specifically planned;
2. cause the implementation thereof and follow up by preparing initial activity plans that the projects shall be guided by and execute and by giving the necessary cognizance to the concerned bodies;

፫ የቋሚ ንብረት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ በአግባቡ ተደራጅቶ ስራውን እስኪረከብ ድረስ፡-

ሀ. የከተማው ቦታዎችና ቤቶች አመዘጋገብና የመረጃ አያያዝ እንዲሁም የይዞታ እና ወይም የባለቤትነት ስም ዝውውር በወጡ ፖሊሲዎችና ህጎች መሰረት በክፍለ ከተማ ደረጃ በስራው መስክ በሚመለከተው አካል በአግባቡ መፈፀሙን ያረጋግጣል፣ ከፖሊስና ከህግ ውጪ የሆኑ የቦታ ወይም የቤት አስተዳደር አፈፃፀም ሲከሰት የማስተካከያ እርምጃ ይወሰዳል፣

ለ. የይዞታ እና ቋሚ ንብረት ምዝገባ እና ጥበቃ አገልግሎቶች ይሰጣል፣ የቦታ ይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤ወቅታዊ የካዳስተር ስርዓት ያደራጃል፤ የመሬት አጠቃቀም ዓይነትና የባለይዞታዎች መረጃዎች ይይዛል፤ይጠብቃል፣ በህግ መሠረት ለህጋዊ ባለይዞታዎች የቦታ አገልግሎት ለውጥ ጥያቄዎች መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፣

ሐ. የመሬት አስተዳደር አፈፃፀም ስርዓቶች የሚመሩባቸውን የአገልግሎት አሰጣጥ መመሪያዎች በጥናት ወቅታዊ ያደርጋል ፣ይተገብራል፣ በስራው መስክ ለሚመለከተው አካል ያስተላልፋል በአግባቡ ተግባራዊ መሆናቸውን ያረጋግጣል፣

መ. ስለይዞታ አስተዳደር የሰጠውን አገልግሎት የሚመለከቱ መረጃዎችን በአግባቡ ይይዛል፤ ያደራጃል ለቋሚ ንብረት ምዝገባና ጥበቃ ተቋም ያስረክባል፣

3. until the Immovable Property Registration and Information Agency is properly organized and takeover the task, the project office shall:-

a. ascertain the proper implementation, at sub-city level by the concerned body in the area, of land and houses registration and information handig of the City as well as possessorial and/or ownership right transfer is in accordance with policies and laws; take corrective measures where the implementation of land or house administration is inconsistent with the policies and law;

b. render service of registration and protection regarding possesstion and immovable property; issue certificate of title deed for land possession; organize current cadastre system; keep and preserve information about type of land usage and possessors thereof; investigate and pass decision on questions of changing land usage by legal possessors of land in accordance with law;

c. update and implement, based on study, directives of service governing the land administration execution system; transfer same to the concerned body in the area of work; ascertain the proper implementation thereof;

d. properly keep and organize data regarding service rendered in relation to land possession administration; handover same to the immovable property registration and preservation institution;

ሠ. የንብረት ዋጋ ስሌት ቀመር ገበያውን ተከትሎ በየወቅቱ ያዘጋጃል፤ የቦታ ኪራይና የቤት ግብር ተመን አስልቶ ለሚመለከተው አካል ያስተላልፋል፣

ረ. ከካሳ ጉዳይ ዉጪ ለግብር፣ ለፍርድ ቤቶችና ለመሳሰሉት የንብረት ግምት አገልግሎት ይሰጣል፤

፬ በህግ የሚቀመጠውን የአሰራር ስርአት ተከትሎ ለሰነድ አልባ ይዞታዎች የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ይሰጣል፤ ማህደራቸውን ያደራጃል፣

፭ በካርታ ዝግጅት ወቅት የሚታዩትን ሽንሻኖዎች ጉድለቶች የቴክኒክ ቡድን በማዋቀር በየጊዜው በመገምገም የጥራት ቁጥጥር ያካሂዳል፤

፮ ንዑስ ፕሮጀክቶቹ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮችና ማነቆዎች ተከታትሎ እንዲፈቱ ያደርጋል፣

፯ የክትትልና ድጋፍ እቅድ በማዘጋጀት የንዑስ ፕሮጀክቶችን የስራ አፈጻጸም ይከታተላል፣ ይገመግማል፣

፰ በከተማ አቀፍ ደረጃ የሽንሻኖ ማስተካከል ፕላን ያዘጋጃል፣ ያስፈቅዳል፤ ሲፈቀድም የይዞታ ማስረጃ በተስተካከለዉ አግባብ ይሰጣል፤ የሊዝ ዉሎችንም በተስተካከለዉ መሠረት ያሻሽላል፡፡

፵ የከተማ ፕላን ኢንስቲትዩት

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩ ል፡-

፩ የከተማዋን መዋቅራዊ ፕላን፣ የአካባቢ ልማት ፕላንና የከተማ ፕላን ስ ንዳርዶችን ያዘጋጃል፣ ወቅ ዊ ያደርጋል፣ ንደአስፈላጊነቱ የፕላን ክለሳ ያካሂዳል፣ ህጉ በሚፈቅደው መሠረት የተዘጋጁ ፕላኖች ንዲፀድቁ ያደርጋል፣

፪ የከተማ ፕላን ለማዘጋጀት የሚያስፈልጉ ሁለገብ ጥናቶችና ምርምሮች ያካሂዳል፣ የአገር ውስጥም ሆነ አለም አቀፍ ተሞክሮዎችን በመሰብሰብና በማደራጀት ጠቃሚ ሃሳቦችን ሥራ ላይ ያውላል፣ በዚህም ዙሪያ የአቅም ግንባ ና የምክር አገልግሎት ይሰጣል፣

e. prepare the current property price statement based on the market; transfer by calculating the land rent fee and house tax statement to the concerned body;

f. provide property valuation service for tax, court and other similar purposes, with the exception of compensation matters;

4. issue title deed for possessions without title deed in accordance with the work rules provided by law; organize the files thereof;
5. perform, by organizing technique team, quality supervision over the discrepancies of parcels during preparation of title deed;
6. follow up and cause the problems and bottle necks encountered by the sub projects resolved;
7. follow up and evaluate work performance of the sub projects by preparing monitoring and support plan;
8. prepare plan of physical regularization at City level; get same permitted; issue certificate of possession in accordance with the change thereof; novate lease contract pursuant to the change.

**40. Urban Plan Institute**

The Institute shall have the following powers and functions:-

1. prepare structural plan, environmental development plan of the City and city plan standards; update the same; conduct plan revision, where necessary; cause plans prepared approved in accordance with the law.
2. conduct comprehensive study and research necessary to prepare city plan; practice important ideas by gathering and organizing international and domestic best experiences; provide capacity building and consultancy service in this area.

፫ የከተማ ፕላኖች አፈፃፀም በፀደቁት ፕላኖች መሠረት መሆናቸውንና የተጠበቀውን ዉጤት ማምጣት መቻላቸዉን ለማረጋገጥ ንዲቻል የአፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ያካሂዳል፣ ለዚህም ተግባር መረጃና ሪፖርቶች ከሚመለከ ቸዉ አካላት ንዲሰጠው ያደርጋል፣ በፕላን ጥሰት ላይ ችግሩን በፈጠሩት አካላት ላይ ርምጃ ይወስዳል፤ ያስወስዳል፣

፬ የፌደራል መንግሥቱ ህግ በሚፈቅደዉ መሠረት ለከተማ ፕላን ባለሞያዎች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ሰርትፊኬት ይሰጣል፣

፭ የማዕድን በ ዎችንና ያላቸዉን ክምችት የሚያሳይ ከተማ አቀፍ ካርታ ያዘጋጃል፤ ያስጸድቃል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

፮ ለከተማ ፕላን ዝግጅትና አፈፃፀም የሚሆን አዋጅ፣ ደንብ፣ ስ ንዳርድ፣ መመሪያ ያዘጋጃል፣ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል::

**፵፩ የተቀናጀ የመሬት መረጃ ሥርዓት ዝርጋ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት**

የፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩ ል:-

ሀ. ከመሬት ልማትና መሬት ነክ ንብረት አስተዳደር ጋር በተያያዘ የሚ የውን የመረጃ አያያዝ፣ አጠባበቅና አመራር ችግሮች ለመፍ ትና በመንግስትም ሆነ በህዝብ መሬትና ገቢ ላይ የሚፈፀም ወንጀልን ለመከላከል በሚያስችል መልኩ የሚደራጅ፣ ወጥና ዘመናዊነትን የተላበሰ፣ በቴክኖሎጂ የተደገፈ፣ ደህንነቱ አስተማማኝ የሆነ የመረጃ ሥርዓት ሥራ አመራር ይዘረጋል፤

ለ. ዲጂ ል መረጃ ንዲሰበሰብና ንዲነሣ፣ የመሬትና የመሬት ነክ ንብረት መረጃ ንዲሰበሰብ፣ የቤት ቁጥርና የመንገድ ስያሜን ባካተተ ሁኔ መረጃ ንዲተነተንና ንዲቀናጅ ያደርጋል፤

3. conduct execution, follow up and evaluation to ensure that execution of plans of the City are in accordance with the approved plans and they have brought about the expected result; to this end it shall cause information and reports submitted to it by concerned bodies; in case of violation of plan take measure upon the violator organs or cause it to be taken;
4. issue professional qualification certificate to urban planning professionals in accordance with law of the Federal Government;
5. Prepare city-wide map indicating areas of minerals and the concentration thereof; get it approved; follow up the execution.
6. prepare proclamation, regulation, standard, directive to be used for preparation and execution of urban plan; implement the same upon approval.

**40. Integrated Land Information System Installation Project Office**

The project Office shall have the following powers and functions:-

a. install information management system, the security of which is reliable, supported by technology and the government, with the view to alleviate the problem of upkeeping, preserving and management of information in relation to the administration of land development and land related properties.
b. cause digital information gathered and taken, land and land related properties information gathered, and information analyzed and integrated in a way including house number and street names.

ሐ. ኮምፒውተራይዝድ የአሰራር ስርዓት ንዲገነባ፣ ንዲጫን፣ ንዲተነተንና የአገልግሎት ጥራቱን በማስጠበቅ በሥራ ላይ ንዲውል ያደርጋል፤

መ. በተበ ተነ መልኩ የሚገኘውንና በጥቅም ላይ ያልዋለውን የመሬትና መሬት ነክ ንብረት አዲስና ነባር መረጃ እንዲጣመርና ተጣርቶ ለዉሳኔ አሰጣጥ በሚያመች መልኩ እንዲደራጅ ያደርጋል፤

ሠ. የሚዘረጋዉን የመሬት አስተዳደርና ቁጥጥር ሥርዓት ዉጤታማነት የሚያረጋግጡ ዑደቶችን ለማስቀጠል የሚያስፈልጉ የፖሊሲ፣ የህግና ስታንዳርድ ማዕቀፎችን እንደየአግባቡ እንዲቀረጹና ሲጸድቅም ከመረጃ ሥርዓቱ ጋር ተቀናጅተዉ ተግባራዊ መሆናቸዉን ይከታተላል፤

ረ. የተሟላ የቤት ቁጥር፣ የመንገድ መለያ ወይም ስያሜ አካትቶ የመሬት መረጃ ሥርዓቱን እንዲደራጅ ያደርጋል፤

ሰ. የሚዘረጋዉ የመረጃ አስተዳደርና ቁጥጥር ሥርዓት ቀጣይነት ባለዉ መልኩ ለተጠቃሚዉ አገልግሎት መስጠት እንዲችል በመስኩ የሰለጠነ የሰዉ ኃይል እንዲዘጋጅ እና ለቀጣይነት አስፈላጊ የሆኑትን ሀርድዌርና ሶፍትዌር እንዲሁም የግንኙነት መረብ እንዲያደራጅ ያደርጋል፤

ሸ. ፕሮጀክቱ ሲጠናቀቅ በተግባር አገልግሎት ንዲሰጥ በማስጀመርና በማለማመድ በቀጣይነት ሥርዓቱን የሚያስፈጽመው አካል የመረጃው አመራር ብቃት ንዲኖረው ድጋፍ ያደርጋል፣

ቀ. ፕሮጀክቱ በሚጠናቀቅበት ጊዜ አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት በማድረግ ለሚረከበው የሚመለከተው የአስተዳደር አካል ዝርዝርና ግልጽ የሆነ የተሟላ የርክክብ ሠነድ በማዘጋጀት በይፋ የፕሮጀክቶቹን የሥራ ሂደት ያጠናቅቃል፤ በተግባር አስፈትኖ ርክክብ ያደርጋል፤ የፕሮጀክት ጽ/ቤቱን በአግባቡ ይዘጋል፣

c. cause computerized system of work built, loaded, analyzed and cause the same implemented without affecting quality of the service.

d. cause new and existing land and land related properties information, which is dispersed and not used, to be unified, checked and organized in a way it is comfortable for decision making.

e. cause framed policy, legal and standard frameworks that are necessary for continuity of the land administration and control system effectiveness assuring circulations; up on approval follow up the implementation of the same being integrated with the information system.

f. cause the land information sytem organized including fulfileged house number, street identification or name.

g. cause prepared human resource trained in the area and the necessary hardware and software as well as communication network organized with the view to enable the information administration and control system serve the customer in sustainable way.

h. provide support, to enable qualified in managing the information at the end of the project, to the body that executes the system in the future by practically training and starting so that the service is rendered.

i. accomplish openly the work process of the projects, at the end of the project, by making the necessary preparation to the concerned overtaking administrative body and preparing specific and clear transfer document; transfer the same by practically examining; properly close the project office.

## ፵፪. የመሬት መረጃና ቴክኖሎጂ ማዕከል

ማዕከሉ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩ የመሬትና መሬት ነክ መረጃዎች ዳታ ቤዝ ወይም ባንክ ያዘጋጃል ያስተዳድራል፤

፪ የመረጃ ልውውጥ አጠቃቀምና አሰባሰብ የሚያገለግል ሲስተም ያጠናል፣ ይዘረጋል፣ በመሬት ልማትና ማኔጅመንት እንዲሁም ማዘጋጃቤታዊ አገልገሎት ውስጥ ላሉት ተቋማት የመረጃ ልውውጡን ለማቀላጠፍና ደህንነቱን ከማረጋገጥ አኳያ ድጋፍ ይሰጣል፤

፫ መሬትና መሬት ነክ የጂኦፊዚካ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ይተነትናል፣ ያደራጃል፣ ወቅታዊ ያደርጋል፣ ያሰራጫል፣ ለዚሁ ሥራ የሚሆን መረጃዎችን ከተለያዩ መሥሪያቤቶች ይሰበስባል ያደራጃል፡፡

፬ መሰረታዊ የከተማ ካርታዎችንና መሬት ነክ መረጃዎችን ለተገልጋዮች አመቺ በሆነ መልክ ያደራጃል ያሰራጫል፤ ለሚሰጠውም፤ አገልግሎት በህግ መሠረት ክፍያ ይሰበስባል፡፡

፭ ከመሬት ነክ መረጃ ጋር የተዛመደ የፌደራልና የከተማዋን ፖሊሲዎች ስልቶች ህጎችና ስታንዳርዶችን በከተማዋ ውስጥ ተግባራዊ መሆናቸውን ያረጋግጣል፡፡

፮ ለመሬት ነክ መረጃ አሰባሰብ አደረጃጀትና አሰረጫጨት የሚሆን አዋጅ ደንብ ስታንዳርድና መመሪያ ያዘጋጃል፤ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

፯ መሬት ተቋማትን አጠቃላይ የመረጃና ቴክኖሎጂ ማዕከል በመሆን በተቀናጀ የመሬት መረጃ ዝርጋታና አያያዝ የሚያራጀውን መረጃ፤ የሲስተም ፕላትፍርምና ቴክኖዎሎጂ በመረከብ ያስተዳድራል፣ የቴክኖሎጂውን እደገትና የአስተዳዳሩን ፍላጎት አቅም መሰረት አድርጎ የመሬት መረጃ ስረአቱንና ቴክኖሎጂውን በየጊዜው እንዲሻሻል ያደርጋል የቴክኖሎጂ ክፍተቶችን ይሞላል፤

## 42. Land Information and Technology Centre

The Centre shall have the following Powers and Functions

1. prepare and administer land and land related information data base or bank.
2. study and install a system that serves information exchange, utilization and gathering; provide support to institutions within municipal service towards fostering the information exchange and ensuring its security.
3. gather land and land related geophysical information; analyze, organize, update and distribute the same; gather information, to this end, from different offices.
4. organize and distribute, in a way comfortable to the customers, base maps and land related information; collect fee for the service it renders in accordance with law.
5. ensure the implementation of the federal and the City's policies, strategies, laws, and standards related to land related information.
6. prepare proclamation, regulation, standard, directive to be used for preparation and execution of urban plan and even for gathering, organizing and distributing land related information; implement the same upon approval;
7. being the center of general information and technology for land institution administer and obtain information ,system platform and technology which it organizes; update land information system and technology based on the development of technology and the city Government's need currently, fill technology gaps

፰ መሬት ተቋማትን አጠቃላይ የመረጃና ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ስታንዳርድ ያወጣል፣ የመጠቀም አቅም ግንባታና ድጋፍ ያደርጋል፡፡ ስታንዳርዱ መጠበቁን ይከታታላል ያስጠብቃል

፱ በአጠቃላይ ለመሬት ነክ ተቋማት የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂና መረጃ ማዕከል በመሆን አገልግሎቶችን ይፈፅማል፣

፲ የመሬት ቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦችን ይተክላል፣ ያስተዳድራል፣ ዘመናዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፣ እንዲሁም ለአየር ካርታ ዝግጅት የሚያስፈልጉ የበረራ መቆጣጠሪያ ነጥቦችን ያዘጋጃል፣ የበረራ ካርታ የሚመራበትን ሥርዓት ይነድፋል፣ ይተገብራል፡፡

## ፵፫ የመንገድና ትራንስፖርት ቢሮ

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩ አንበሳ የከተማ አውቶቢስ ድርጅትን፣ የአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ባለሥልጣንን፣ እንዲሁም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከሚመለከተው አካል በሚሰጥ ውክልና መሠረት የአዲስ አበባ ትራንስፖርት ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤትንና የትራፊክ አስተዳደር ክፍልን በበላይነት ያስተዳድራል፣ ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣

፪ በከተማው ደህንነቱ የተረጋገጠ፣ ቀልጣፋና የተመጣጠነ የትራንስፖርት አገልግሎት መኖሩን ያረጋግጣል፣

፫ የትራንስፖርት አገልግሎት ፍላጎትና አቅርቦት፣ ሥርዓት እንዲሁም የትራፊክ አመራር በተመለከተ ወቅታዊ ጥናት በማካሄድ የሚሻሻልበትን ሥልት ይቀይሳል፣

፬ በከተማው ትራንስፖርትን በተመለከተ ተገቢውን መረጃ ያደራጃል፣ የትራንስፖርት አገልግሎቱ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መደገፉን ያረጋግጣል፣

፭ የከተማውን የትራንስፖርት ፕላንና ፕሮግራም ከከተማው የመሬት አጠቃቀም ሥርዓት ጋር አጣጥሞ ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፣

8. make general land institution of information and technology standard utilization.
9. perform generally to land and land related institution being information communication technology and information center;
10. erect land survey control points; administer and update same; prepare flight control points necessary for airal map preparation; design system by which flight map is guided; implement same.

## 43. Road and Transport Bureau

The Bureau shall have the following powers and functions:-

1. superiorly administer, direct and control the Anbesa City Bus Enterprise, the Addis Ababa Roads Authority; as well the Addis Ababa Branch Transport Office, and the Traffic Management Department based on delegation, where necessary, of the concerned body;
2. ensure the existence of secured, expedient, and balanced transport service within the City;
3. devise mechanism for the improvement of transport service demand and supply, system as well management by conducting timely studies;
4. organize necessary data related to transport in the City; ensure that the transport service is supported by information technology;
5. prepare transport plan and program in consistence with the land use system of the City; implement same upon approval; based on the delegation from the concerned body ensure that roads are constructed accordingly;

፯ በትራፊክ ደንብ ተላላፊዎች ላይ በህግ መሠረት የሚጣል ቅጣት ራሱ ወይም ዉክልና በሚሰጠዉ ተቋም አማካይነት በከተማዉ አስተዳደር የፋይናንስ ህግ መሠረት ይሰበስባል፤ የተሰበሰበዉንም ለከተማ አስተዳደሩ ግምጃ ቤት ፈሰስ ያደርጋል፤

፯ ከሚመለከተዉ አካል በሚሰጠዉ ዉክልና መሠረት የከተማዉን ትራፊክ አመራርና አስተዳደር ሥራ ይፈጽማል፤ በበላይነት ይቆጣጠራል፤ ለአገልግሎቱ ስልጠት የሚያግዙ ሥልቶችን ይቀይሳል፤

፰ በህግ መሠረት ተሽከርካሪዎችን ይመዘግባል፣ ባለቤትነት ሲተላለፍ ህጋዊ መሆኑን በማረጋገጥ ይመዘግባል፣ ከዚህ ጋር የተያያዙ የአገልግሎት ክፍያዎችን ይሰበስባል፤

፱ የተሽከርካሪ ዓመታዊ ምርመራ በራሱ ወይም በህግ አግባብ ዉክልና በሰጠዉ ተቋም አማካይነት ያካሂዳል፤ የህዝብን ደህንነት የሚጎዱ ተሽከርካሪዎች ላይ ተገቢዉን እርምጃ ይወስዳል፤

፲ በህግ መሠረት የአሽከርካሪነት ብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፤ ያድሳል፤ የአገልግሎት ክፍያ ይሰበስባል፤

፲፩ የባለሞተር ተሽከርካሪዎችን የማሽከርከር ሥልጠና ለሚሰጡ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች የሥራ ፈቃድ ይሰጣል፤ ይቆጣጠራል፤ አግባብነት የሌለዉ ተግባር ሲፈጽም ተገቢዉን እርምጃ ይወስዳል፤

፲፪ ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በመተባበር በትራንስፖርት ዘርፍ የሚሰማሩ ማህበራት እንዲደራጁና እንዲጠናከሩ ተገቢዉን ድጋፍ ይሰጣል፤ ማህበራቱም ለከተማዉ ትራንስፖርት ቅልጥፍናና ደህንነት መሥራታቸዉን ያረጋግጣል፤

፲፫ በትራንስፖርትና በጋራዥ አገልግሎት ለሚሰማሩ ግለሰቦችና ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፤ ይቆጣጠራል፤

6. collect fine, by itself or through the institution so authorized, imposed upon violators of traffic regulation by law in accordance with the finance law of the City; deposit, what is so collected, into treasury of the City Government;
7. based on delegation of the concerned body perform the traffic management task of the City; superiorly control same; devise techniques for the effectiveness of the service;
8. register vehicles in accordance with law; in cases of transfer of ownership register same upon ensuring the legality; collect fees related to such service;
9. undertake annual inspection of vehicles by itself or through the institution authorized in accordance with law; take necessary measure on vehicles harmful to the society;
10. issue driving license in accordance with the law; renew same; collect service charge thereof;
11. issue working license to individuals or organizations involved in training the skill of driving motor vehicles; control same; take appropriate measure where they perform inappropriately;
12. provide appropriate support in the formation and strengthening of associations involved in the transport sector in cooperation with the concerned bodies; ensure that the associations work towards effectiveness and security of transport in the City;
13. issue certificate of proficiency to individuals and organizations involved in transport and garaj service ; control same ;

www.chilot.me

፲፬ በከተማዉ አስተዳደር ለተሽከርካሪዎች አገልግሎት የሚዉሉ መናኸሪያዎችንና ፌርማታዎችን ይገነባል፤ ያስተዳድራል

፲፭ የከተማዉን የትራንስፖርት መሠረተ ልማት ይገነባል፣ ያስፋፋል፣ ይጠግናል፣ ያስተዳድራል፤

፲፮ ስለ ከተማዉ ትራንስፖርት አገልግሎት እንዲሁም የትራፊክ ሥርዓት ለሚመለከታቸዉ አካላት ሥልጠና ይሰጣል፡፡

## ፵፬ የአዲስ አበባ መንገዶች ባለሥልጣን

፩. በዚህ አዋጅ የተደነገገው ንደተጠበቀ ሆኖ የመንገዶች ባለሥልጣን በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፯/፲፱፻፺፯ ዓ.ም. የተወሰነው ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩ ል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው ንደተጠበቀ ሆኖ ባለሥልጣኑ፣

ሀ. አዳዲስ መንገዶች ሲሰሩም ሆነ ነባር መንገዶች ሲስፋፉ ለአረንጓዴ ቦ በቂ ቦ መከለሉን ያረጋግጣል፤

ለ. በዋና ዋና መንገዶችና በመለስተኛ ዋና መንገዶች ግራና ቀኝ ወይም በደሴቶች ላይ የሚተከሉ ዛፎችን አይነትና
መጠን ወስኖ ለውበት መናፈሻ ፓርክና ዘላቂ ማረፊያ ልማትና አስተዳደር ኤጀንሲ ያስ ዉቃል፤

ሐ. የአሽከርካሪዎችን የርቀት ይ የሚጋርዱ ወይም የደረቁ የመንገድ ዳርና የአደባባይ ዕፅዋት ንደአስፈላጊነቱ በውበት መናፈሻ ፓርክና ዘላቂ ማረፊያ ልማትና አስተዳደር ኤጀንሲ ንዲወገዱ ወይም ንዲመለመሉ ያስደርጋል፤

መ. የመንገድ አካፋዮችና ዳርቻዎች፣ የመከለያ አጥሮች ደረጃና ዲዛይን ያዘጋጃል ሲበላሹና ጉዳት ሲደርስባቸው በተቀመጠላቸው ደረጃ መሠረት ይጠግናል፡፡

14. cause the construction and administer terminals and vehicle stop points within the City Government ;
15. construct, expand, maintain and administer the transport infrastructure of the City;
16. offer training on transport service of the City as well traffic system to the concerned bodies.

## 44. Addis Ababa Roads Authority

1. without prejudice to the provisions of this Proclamation the Addis Ababa Roads Authority shall have the powers and functions stated under the Addis Ababa City Council Regulations No. 7 of 1997;
2. without prejudice to the provisions of Sub-Article(1) of this Article, the Authority shall:
   a) ensure the designation of adequate green area during construction of new roads and expansion of existing roads;
   b) identify, determine and notify to the Beautification, Parks and Cemetry Development and Administration Agency the type and quantity of trees to be planted to the sides of major and sub-major roads or on road junctures;
   c) cause the Beautification, Parks and Cemetry Development and Administration Agency to remove or pick as appropriate road side or juncture trees that impede sight at distance to drivers or dried up;
   d) establish standards and designs for road partitions, junctures and fences; repair in accordance with the standard when destroyed and damaged.

## ፵፭. የሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮ

ቢሮዉ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩ ል:-

፩ ፖሊሲዎችና ሕጎች በከተማዉ አስተዳደር ሲተገበሩ የሴቶችን፣ የሕጻናትንና የወጣቶችን ሁለንተናዊ መብትና ደህንነት የሚጠብቁ መሆናቸዉን ይከታተላል፣ በአስተዳደሩ ሥር በሚገኙ በሁሉም አስፈጻሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት እንዲሁም ሌሎች የአስተዳደሩ አካላት የሥርዓተ ጾታንና የወጣቶችን ጉዳይ በዕቅዳቸው ላይ ማካተታቸውን ይከታተላል፤

፪ የሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች መብቶች ስለመጣሳቸው መረጃ ሲደርሰው ጉዳዩን ከሚመለከተዉ አካል ጋር በማጥናትና በማጣራት በሚመለከተው አካል በኩል ተገቢው መፍትሔ እንዲሰጥ ያደርጋል፤

፫ በሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይና በሥርዓተ-ፆታ እኩልነት ዙሪያ ግንዛቤና ንቅናቄ እንዲፈጠር ያደርጋል፤

፬ የሴቶችና የወጣቶችን ዐቅም የሚያጎለብቱ ትምህርታዊ፣ ሙያዊና የተጨማሪ ክህሎት ሥልጠናዎችን ያዘጋጃል፣ ይሰጣል፤

፭ አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ሴቶችና ወጣቶች በማህበራት ንዲደራጁና የብድርና የቁጠባ አገልግሎት ንዲያገኙ ሁኔ ዎችን ያመቻቻል፤

፮ ለሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች መብትና ደህንነት የሚሰሩ ማህበራት ንዲደራጁና ንዲጠናከሩ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፤

፯ ሴቶችና ወጣቶች በከተማዉ አስተዳደር የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ንቅስቃሴዎች ውስጥ በንቃት ንዲሳተፉና ተጠቃሚ ንዲሆኑ ከሚመለከ ቸው አካላት ጋር በጥምረት ይሰራል፣

## 45. Women Children and Youth Affairs Bureau

The Bureau shall have the following powers and functions:-

1. follow up whether the overall rights and security of women, children and youth are respected in the implementation of policies and law in the City Government; follow up that gender and youth issues are included in the plans of the executive and municipal service organs and other organs of the City Government;
2. conduct investigation, in cooperation with the concerned bodies, upon receiving compliant of violation of the rights of women, children and youth and ensure that measures are taken by the appropriate organ;
3. cause mobilization and awareness created regarding women, children and youth affairs and gender and equality;
4. organize and provide educational, professional and additional skills training that strengthen the capacity of women and the youth;
5. facilitate the establishment of women youth organizations and their access to credit and saving services in collaboration with appropriate organs;
6. provide the necessary support for the establishment and strengthening of associations advocating for the rights and welfare of women, children and the youth;
7. work in coordination with concerned bodies to enable women and the youth effectively participate in and benefit from political, economic and social activities of the City Government;

፰ ሴቶችን ህጻናትንና ወጣቶችን በሚመለከት ከልማት ስትራቴጂ አኳያ ተቃኝቶ በወጣ ፕሮጀክት ላይ በከተማው ውስጥ ከሚሰሩ የተለያዩ መንግስ ዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር ስምምነት ይመሠር ል፤ አፈጻጸማቸዉን ይከታተላል፤ ለሚመለከተዉ አካል ሪፖርት ያቀርባል፤

፱ የሴቶች፣ የሕጻናትና የወጣቶች ማህበራዊ ችግሮች በሁሉም የተባበረ ጥረት መፍትሔ ንዲያገኝ፣ ያስተባብራል፣ ተፈጻሚነቱን ይከ ተላል፤

፲ ለአካል ጉዳተኛ ሴቶችና ወጣቶች ልዩ ትኩረት በመስጠት በሁሉም የልማት ሥራዎች ከግምት ውስጥ እንዲገቡ ለማድረግ፣ ከተለያዩ ጥቃት መከላከል፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጥቅሞቻቸውን ለማስከበር ከሌሎች አካላት ጋር በትብብር ይሠራል፤

፲፩ በአስተዳደሩ ዉስጥ የሴቶች ልዩ ድጋፍ መብት በአግባቡ ሥራ ላይ ንዲዉል ስልት ይቀይሳል፤ አፈጻጸሙን ይከ ተላል፤

፲፪ የችግረኛ ሴቶችን የኑሮ ሁኔ የሚሻሻልበትን ያጠናል፤ ከሚመለከ ቸዉ አካላት ጋር በመተባበር ተግባራዊ ያደርጋል፤

፲፫ የአስተዳደሩን የወጣት ማዕከላት ንዲሁም የህጻናት ማሳደጊያ ተቋማትን ያስተዳድራል፣ ይመራል፣ እንዲስፋፉና አቅማቸዉ እንዲገነባ ያደርጋል።

## ፵፮ የባህልና ቱሪዝም ቢሮ፣

ቢሮው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩ ል:-

፩ በከተማው ውስጥ የሚገኙ ሪካዊ ቅርሶችን ያጠናል፣ በሕግ መሠረት ይጠብቃል፣ ያስጠብቃል፤ የሀገሪቱ ብሔር ብሔረሰቦች ሪክና ባህል ተመዝግቦ ንዲያዝ ያደርጋል፣ የባህል ሙዚየሞችን ያደራጃል፣ ያስተዳድራል፤ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፎች ንዲዳብሩ ያደርጋል፤

፪ በባህል ተፅዕኖ ሳቢያ ማህበራዊ ዕድገትን የሚያጓትቱ አመለካከቶችን፣ ምነቶችንና ልማዳዊ አሠራሮችን የመለወጥ ተግባሮችን ያከናውናል፤

8. establish agreement with different Non-Governmental organizations operating in the City on women, children and youth related projects that are formulated from the perspective of the development strategy; follow up the implementation thereof; submit report to the concerned body;
